# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በንግድ ሚኒስቴር ቀጥተኛ ክትትል የሚደረግባቸው

# የግብርና ምርቶች የውጭ ንግድ ማስፋፊያ ሥርዓት አፈጻጸም

# እና ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ

# የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ሚያዝያ 2004ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

የንግድ ሚኒስቴር አመሰራረት ........ 1

የንግድ ሚኒስቴር ዓላማ ........ 1

የንግድ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር ........ 2

የንግድ ሚኒስቴር ደርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል ........ 4

የንግድ ሚኒስቴር የፋይናንስ ምንጭ ........ 5

የኦዲቱ ዓላማ ........ 5

የኦዲት ወሰንና ዘዴ ........ 5

የኦዲት አካባቢ(Audit  Area) ........ 6

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች(Audit Issues) ........ 6

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ........ 7

የምርት ገቢያ ማስፋፋት የሥራ ሂደት መግለጫ/System description/ ........ 7

ክፍል ሁለት ........ 14

የኦዲት ግኝቶች ........ 14

ሀ. ለዓለም ገቢያ በሚቀርቡ የግብርና ምርቶች ከምርት ሂደት እስከ ግብይት የሚደረግ የጥራትና የቁጥጥር፣ የክትትልና የድጋፍ ሥርዓት ........ 14

ለውጭ ሀገር ገቢያ በሚቀርቡ የግብርና ምርቶች ላይ የሚደረግ የጥራት ቁጥጥርን በተመለከተ ........ 14

ለውጭ ሀገር ገቢያ የሚቀርቡ የግብይት አዋጅና ደንብ ያልወጣላቸው የግብርና ምርቶች የግብይት ስርዓትን በተመለከተ ........ 16

ወደ ወጭ የሚላኩ የግብርና ምርቶች ላይ ስለሚሰሩ የጥራትና ደረጃ ማዕከላትን በተመለከተ ........ 17

የኢትዮጵያ ምርት ገቢያ ደርጅት ወደ ወጭ ገቢያ የሚላኩ የግብርና ምርቶችን ለሚያመርቱ አርሶ አደሮች እና የግብርና ባለሙያዎች የሚሰጠውን የጥራት ግብረ መልስ አሠራር በተመለከተ ........ 18

ወደ ወጭ ሀገር በሚላኩ የግብርና ምርቶች የገቢያ ሥርዓት ችግሮች ላይ የሚካሄደውን ስራ በተመለከተ ........ 19

ወደ ወጭ ሀገር ገቢያ ሊላኩ ለሚችሉ የግብርና ምርቶች ገቢያ የማፈላለግ ሥርዓት ወደ ዘመናዊ የግብይት ስርዓት ያልገቡ የግብርና ምርቶች አዲስ ገቢያ ማፈላለግን በተመለከተ ........ 21

ወደ ውጭ ገቢያ በሚቀርቡ ዋና ዋና የግብርና ምርቶችን አስመልክቶ የገቢያ ፍላጎት እና የዋጋ
ትንቢያ መካሄዱን በተመለከተ፣ ........................................ 22

ሐ የንግድ ሚኒስቴር የመረጃ አያያዝና ስርጭት ስርዓት ........................................ 23

የግብርና ምርቶች የውጭ ሀገር ግብይት በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት መደገፉን በተመለከተ ........................................ 23

መ.የውጭ ንግድ ማስፋፋያ ጉዳይ የሚመለከታቸው አካላት መካከል ያለው ቅንጅታዊ አሰራር፤ ........................................ 25

የንግድ ሚኒስቴር ከክልል የኤክስፖርት ድጋፍ ኮሚቴዎች ጋር ስለሚያካሂደው
ቅንጅታዊ አሰራር በተመለከተ፡ ........................................ 25

የግብርና ምርቶች የውጭ ንግድን በጥራት ለማቅረብ የሚያግዙ የጂኢያ እና የፒፒ
ከረጢት ለአምራቾች ማቅረብን በተመለከተ፤ ........................................ 26

ወደ ውጭ ሀገር ገቢያ የሚላኩ የግብርና ምርቶች የህገ-ወጥ ግብይት ቁጥጥርን በተመለከተ፣ ........................................ 27

ክፍል ሦስት ........................................ 29

መደምደሚያ ........................................ 29

ክፍል አራት ........................................ 31

የማሻሻያ ሃሳብ ........................................ 31

አባሪ ........................................ I-VII

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

## የንግድ ሚኒስቴር አመሰራረት

1. ቀድሞ የንግድ፣ኢንዱስትሪ እና ቱሪዝም ሚኒስቴር በመባል ይታወቅ የነበረው መ/ቤት የአገር ውስጥ ንግድ ሚኒስቴር፣ የውጭ ንግድ ሚኒስቴር፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የቱሪዝም ኮሚሽን በሚል በአራት መ/ቤቶች ተከፋፍሎ እንዲዋቀር ተደረጎ ነበር፡፡

2. የአገር ውስጥ ንግድ ሚኒስቴር እና የውጭ ንግድ ሚኒስቴር እንደገና በ1983 ዓ.ም የንግድ ሚኒስቴር በሚል ስያሜ እንዲዋሃድ የተደረገ ሲሆን፣ በ1987 ዓ.ም ደግሞ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በአዋጅ ቁጥር 4/1987 በማዋሃድ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚል ስያሜ እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ ይህ መ/ቤት በ1994 ዓ.ም አሥር ተጠሪ መ/ቤቶችን በሥሩ ይዞ እንዲያስተባብርና እንዲመራ በአዋጅ ቁጥር 256/1994 በአዲስ መልክ ተደራጅቶ ነበር፡፡ ሆኖም እንደገና በአዋጅ ቁጥር 411/1996 የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሥሩ አምስት መ/ቤቶች ለእርሱ ተጠሪ ሆነው እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡

3. በአሁኑ ወቅት የቀጣዮቹን አምስት ዓመታት መሰረታዊ የዕቅድ ዓላማዎች፣ የማክሮ ኢኮኖሚ እና የዋና ዋና ዘርፎች ግቦችን፣ የአቅም ግንባታና የመልካም አስተዳደር ተግባሮችን እውን ለማድረግ የፌዴራል አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀቶችን፣ሥልጣንንና ተግባርን ለመወሰን በወጣው አዋጅ 691/2003 የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚል ስያሜ በጋራ ሲሰሩ የነበሩ የሥራ ዘርፎች በሁለት ሚኒስቴር መ/ቤቶች በተናጠል እንዲደራጁ ተደርጎ የንግድ ሚኒስቴር መ/ቤት ለብቻው ተቋቁሟል፡፡

## የንግድ ሚኒስቴር ዓላማ

- የንግድ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 691/2003 መሠረት የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

- ግልጽነትን፣ ተደራሽነትንና ውድድርን መሰረት ያደረገ ሸማቹን፣ የንግዱን ማህበረሰብና አምራቹን ያረካ የተረጋጋ ገበያና ፍትሃዊ የንግድ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ፤
- ሀገሪቱን ከዓለም አቀፍ የንግድ ሥርዓቱ ተጠቃሚ እና ተዋናይ በማድረግ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ግኝትን ማሳደግ፤
- የሚኒስቴር መ/ቤቱን ተልዕኮ ለማሳካት በሚያስችል ደረጃ የማስፈጸም አቅምን ማጎልበት፤

# የንግድ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር

4. የንግድ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር በአዋጅ ተሰጥቶታል፡-

- የአገሪቱ የውጪ ንግድ የሚሰፋፋበትንና ያሚጠናከርበት ሁኔታ ያመቻቻል፣ ለላኪዎች ድጋፍ ይሰጠል፤
- የወጪና የገቢ ዕቃዎች በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ወይም ስለመገዛታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ክትት ያደርጋል፣ ዋጋ አሳንሰው በሚልኩ ወይም በሚያስመጡ ላይ በህግ አግባብ እርምጃ ይወሰዳል፤
- የውጭ ንግድ ግኑኝነቶችን ይመሠርታል፣ የንግድ ድርድሮችን ያስተባብራል፣ ስምምነቶች ይፈራረማል፣ ያስፈጽማል፤
- ፀረ-ውድድር ተግባራትን ለመከላከል የሚያስችል የተሟላ ሥርዓት ይዘረጋል፣አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ በህግ አግባብ ለሸማቾች ጥበቃ ያደርጋል፤
- አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠርት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ የተሰጡ የንግድ ሥራ ፈቃዶች ለተሰጡበት ዓላማ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤
- የሀገር ውስጥ ንግድ እዲስፋፋና ህጋዊ የንግድ አሠራር እዲሰፍን ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎችን ይወስዳል፤
- የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ዋጋ እያጠና ለሚኒስቴሮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀዱም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

- የሀገሪቱን ህጋዊ ስነልክ ሥርዓት ይዘረጋል፣ መተግበሩን ይቆጣጠራል፣ የሚመለከታቸውን አስፈጻሚ አከላት ያስተባብራል፣

- የወጪና የገቢ ንግድ ዕቃዎችን ጥራት ይቆጣጠራል፤ ተፈላጊውን የደረጃ መሥፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ያግዳል፤ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በትብብር ይሰራል፤

- አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ይቆጣጠራል፤ ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ ይወስዳል፤

- በሌሎች አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች የሚሠራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ ያደርጋል፤በአፈጻጸም ላይ የሚወያይ ጉባዔ ይጠራል፣መድረክም ይመራል፤

- የሀገሪቱን የንግድ መረጃዎች ያደራጃል ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤
- የሸማቾችን ጨምሮ የህብረት ሥራ ማህበራት እና የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፡፡

- በተጨማሪም ለቀድሞው የግብርና ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩና በፌዴራል አስፈጻሚ ኣካላት አደረጃጀት የግብርና ምርት ግብይትን በሚመለከት ወደ ንግድ ሚኒስቴር የተሰጡ ተግባሮች የሚከተሉትን ያካትታል፡-

    - ገበሬዎች አርብቶ አደሮችና በግብርና ልማት የተሰማሩ ኢንቬስተሮች በዋጋና በጥራት ተወዳዳሪ ሊሆኑባቸው የሚችሉ የግብርና ምርቶችን በዓለም ገበያ በቅርብ እየተከታተለ የተሟላ ወቅታዊና ትክክለኛ የገበያ መረጃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

    - ዋና ዋና የግብርና ምርቶችን የወደፊት የገበያ ፍላጎትና ዋጋ ትንበያ ጥናት ያካሂዳል፣ውጤቱንም ለሚመለከታቸው ያሰራጫል፤

    - የግብርና ምርቶች ጥራት እንዲጠበቅ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ምክርና ድጋፍ ይሰጣል፤

- የግብርና ምርቶች ጥራትና ተወዳዳሪነት ለመጠበቅ የሚያስችል የግብይት ሥርዓት እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- በዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 372/1996 የተደነገገው የግብርና ምርቶች ግብይት ሥርዓት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የግብርና ምርቶች የግብይት ማዕከላት እንዲፈጠሩና እዲጠናከሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የኤክስፖርት ገበያ መዳረሻ ሀገሮችን እንቅስቃሴ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
- የገበያ መረጃ አቅርቦቱን ሥርዓት ለማጠናከር የሕብረት ሥራ ማህበራትና የግል ባለሀብቶችን ተሳትፎ ያበረታታል።

## የንግድ ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

5. የንግድ ሚኒስቴር በአንድ ሚኒስትር እና በሁለት ሚኒስትር ዴኤታ የሚመራ ሆኖ በሁለት ዋና ዘርፎች የንግድ ማስፋፊያ ዘርፍ እና የንግድ አሰራርና ሬጉላቶሪ ዘርፍ ተዋቅሯል፡፡ ለንግድ ማስፋፊያ ዘርፍ ተጠሪ የሆኑት ዳይሬክቶሬቶች የንግድ ግንኙነትና ድርድር ዳይሬክቶሬት፣ የግብርና ምርቶች ግብይት መረጃና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት፣ የግብርና ምርት ግብይት ዳይሬክቶሬት ናቸው፡፡ የንግድ አሰራርና ሬጉላቶሪ ዘርፍ ተጠሪ የሆኑት ዳይሬክቶሬቶች የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክቶሬት፣ የኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት፣ የቴክኒክ ደንብ ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት፣ የወጪና ገቢ ምርቶች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ናቸው፡፡ በድጋፍ ሰጪ ዳይሬክቶሬቶች ደግሞ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት፣ የህግ ዳይሬክቶሬት፣ የኦዲት ዳይሬክቶሬት፣ የፋይናንስና አቅርቦት ዳይሬክቶሬት፣ የአሰራር ማሻሻያና የሰው ሀብት ዳይሬክቶሬት፣ የዕቅድና የመረጃ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት፣ የሴቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት አሉት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በድሬዳዋ ላይ እና አራት ተጠሪ ተቋማት ማለትም የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን፣ የንግድ አሰራር እና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን፣ የህብረት ሥራ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ በማካተት እንዲዋቀር ተደርጓል፡፡
6. አሁን ባለው አደረጃጀት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሰው ሀብት ፍላጎቱ 620 ሲሆን ከዚህም ውስጥ 260(41.94%) በሰው ኃይል የተሞላ ሲሆን፣ 360(58.06%) ክፍት መደቦች ይገኛሉ(አባሪ1 )፡፡

## የንግድ ሚኒስቴር የፋይናንስ ምንጭ

7. የንግድ ሚኒስቴር መ/ቤት በአዋጅ በተቀመጠው መሠረት ሥራውን ለማከናወን ከመንግስት በጀት የሚመደብለት ሲሆን፣ በ2001 በጀት ዓመት 16,693,900.00፣ በ2002 በጀት ዓመት 15,778,575.00 እና በ2003 በጀት ዓመት 16,624,280.00 ብር ለሚያከናውናቸው ተግባራት ማስፈጸሚያ የሚያውለው በጀት ተመድቦለታል፡፡ ከተመደበለት በጀት ውስጥ በቅደም ተከተሉ መሠረት ብር 13,541,700.02(81.12%)፣ ብር 14,231,130.99 (90.19%) እና ብር 13,443,605.80(80.87%) ሥራ ላይ አውሏል፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

8. የኦዲቱ አላማ በንግድ ሚኒስቴር ቀጥተኛ ክትትል የሚደረግባቸው የግብርና ምርቶች የውጭ ንግድ ማስፋፊያ ሥርዓት በአግባቡ የተዘረጋ አፈጻጸሙ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ለመገምገም ሲሆን ይህንን በተመለከተ የሚታዩ የአሰራር ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳቦችን /Recommendations/ ለመስጠት ነው፡፡

## የኦዲት ወሰንና ዘዴ

9. ኦዲቱ የሸፈነው ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ በንግድ ሚኒስቴር ቀጥተኛ ክትትል የሚደረግባቸው የግብርና ምርቶች የውጭ ንግድ ገበያ ማስፋፊያን በተመለከተ የተከናወኑ ሥራዎችን ነው፡፡ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በንግድ ሚኒስቴር ሆኖ በኦሮሚያ ክልል ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ እና በስሩ በሚገኙ በናሙና በተመረጡ አራት ዞኖችና ሶስት ወረዳዎች እንዲሁም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ግብይትና የህብረት ሥራ ኤጀንሲ እና በስሩ በሚገኙ በናሙና በተመረጡ ሶስት ዞኖች እና አራት ወረዳዎች ያካተተ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከአስራ ሁለት ላኪዎች/Exporters/ ጋር ቃለ-መጠይቅ በማካሄድ እና ለአስራ ስምንት ላኪዎች መጠይቅ/Survey Questionners/ በመላክ መልስ እንዲሰጡ የተደረገ ሲሆን ከአስራ ሰባቱ ላኪዎች ጋር የፊትለፊት ወይይት/focus group discussion/ ተደርጓል፡፡

10. በዚህም መሠረት በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በናሙና በተመረጡ የኦሮሚያ እና የደቡብ ክልል ቢሮዎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ከውጭ ንግድ ገበያ ማስፋፊያ ጋር ተያያዥ የሆኑ እና አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመከለስ፣ የግብይቱን ሂደት በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት

ማዕከላት በአካል ተገኝቶ በማየት፤ ከላኪዎች በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ ትንተና በማካሄድ እንዲሁም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በናሙና ለተመረጡ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ ለዝርዝር ኦዲቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## የኦዲት አካባቢ(Audit Area)

11. በኦዲቱ የተለየው የኦዲት አከባቢ፡- በንግድ ሚኒስቴር ቀጥተኛ ክትትል የሚደረግባቸው የግብርና ምርቶች የውጭ ንግድ ማስፋፊያ ሥርዓት አፈጻጸም እና ውጤታማነትን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች(Audit Issues)

12. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አከባቢ ስር አራት የኦዲት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተለይተዋል፡፡ እነርሱም:-

1. ለዓለም ገበያ ሊላኩ የሚችሉ የግብርና ምርቶች ላይ ቁጥጥር፣ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል ያሠራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን እና አፈፃፀሙን መገምገም፤
   - 1.1 ወደ ውጭ በሚላኩ የግብርና ምርቶች ላይ የሚደረገውን የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓትን መገምገም፤
   - 1.2 ወደ ውጭ በሚላኩ የግብርና ምርቶች ላይ የሚደረገው የድጋፍ ሥርዓትን መገምገም፤
2. ለዓለም ገበያ ሊላኩ ለሚችሉ የግብርና ምርቶች የውጭ ሀገር ገበያ ለማፈላለግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን፣ አፈፃፀሙን እና ውጤታማነቱን መገምገም፤
3. ለዓለም ገበያ ሊላኩ የሚችሉ የግብርና ምርቶች የመረጃ አያያዝና ስርጭት ሥርዓት መገምገም፤
4. የውጭ ንግድ ማስፋፊያ በተመለከተ ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት መካከል ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር መገምገም፣

ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

13. ከላይ ለተመረጡት አራት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) ለመመዘን የሚያስችሉ አርባ (40) የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ተያይዘዋል፡፡

## የምርት ገበያ ማስፋፋት የሥራ ሂደት መግለጫ /Process description/

**ለዓለም ገበያ የሚላኩ ግብርና ምርቶች ግብይት ጥራት ቁጥጥር እና መረጃ አያያዝ**

14. የግብርና ምርቶች በአግባቡ እንዲመረቱ በግብርና ልማት ባለሙያዎች ክትትል ተደርጎበት የተመረተው ምርት በተዘጋጀላቸው ጆኒያ ወይም ሌሎች ዕቃዎች አማካይነት ለሽያጭ ወደ ግብይት ማዕከላት ይቀርባሉ፤

የልማት ጣቢያ ሰራተኞች በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት በመገኘት ለገበያ የቀረበውን የግብርና ምርቶች ጥራት ይመረምራሉ፣ የግብይት ተዋንያኖችን ህጋዊነት ያጣራሉ እንዲሁም አቅራቢዎችና ማኅበራት ለምርት ግዥ የሚጠቀሙባቸው ሚዛኖች በሚመለከተው አካል የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣሉ፤

የልማት ጣቢያ ሰራተኞች የግብርና ምርት አምራቾች ምርት ሳይደርስ ለገበያ እንዳያቀርቡ ለመከላከል ክትትል ያደርጋሉ፤

የልማት ጣቢያ ሰራተኞች በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ተሳታፊ የሚሆኑት አምራች አርሶ አደሮች፣ አልሚ ባለሀብቶች፣ የሕብረት ሥራ ማኅበራትና ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው አቅራቢዎች/ወኪሎቻቸው/ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፤

የልማት ጣቢያ ሰራተኞች በግብይት ማዕከላቱ የምርት ግዥ የሚያከናውኑ አቅራቢዎችና የሕብረት ሥራ ማህበራት የሚገለገሉባቸው ሚዛኖች የተመረመሩና ከሚመለከተው አካል የብቃት ማረጋገጫ ያላቸው መሆኑን፣ የሚገዙትን ምርቱን ለመያዣነት የሚጠቀሙባቸው ጆንያዎች ለዚሁ አገልግሎት ብቻ የተመረቱና ንጽህናቸው የተጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣሉ፤

የልማት ጣቢያ ሰራተኞች በግብይት ማዕከላቱ የሚከናወነው የምርት ግዥና ሽያጭ ክልሉ ባስቀመጠው አሠራር መሠረት ሥርዓት ይዞ መፈፀሙን ይቆጣጠራሉ፤

የወረዳ የግብርና ምርት ጥራት ተቆጣጣሪ አልሚ ባለሀብቶች በግል እርሻቸው ከአመረቱት ውጭ የተዘጋጀ ምርት አለመግዛታቸውን ይከታተላሉ፣

የመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት

15.የወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት የግብርና ምርት ማዘጋጃ እንዱስትሪዎች በተሰጣቸው የብቃት ማረጋገጫ መሠረት ለሥራ ዝግጁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

የወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት እያንዳንዱ አቅራቢና የሕብረት ሥራ ማነበር በግብይት ማዕከላቱ በመገኘት በየእለቱ የገዛውን የቡና መጠን መዝግቦ በመያዝ የተገዛው ቡና ሳይባክን ወደ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች መድረሱን ይቆጣጠራል፣

የወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት በአምራች አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱ፣ ከተከለሉ የግብይት ማዕከላት ውጭ ቡና የሚገዙና የሚያንቀሳቅሱ ሕገወጦችን ተከታትሎ ለሕግ እንዲቀርቡ ያደርጋል፣

የልማት ጣቢያ ሰራተኞች በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል ውስጥ በአርሶ አደሩና በቡና አቅራቢዎች መካከል የሚካሄደው ግብይት በህጉ መሰረት መከናወኑን ይከታላሉ፤

የልማት ጣቢያ ሰራተኞች በመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል ውስጥ በእያንዳንዱ የቡና አቅራቢ የተገዛውን የቡና ዓይነትና መጠን በሚመለከት መረጃ በማሰባሰብ ለወረዳ የግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ያስተላልፋሉ፤

ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት በመጀመሪክ □ረጃ የቡና ግብ□ት ማ□ከላት የሚከናወን የእሸትና የጀን□ል ቡና መሸጫ ዋጋን በማሰባሰብ ያደራጃሉ፣

የቡና አቅራቢዎችና ማኅበራት ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የገዙትን እና የቡና አልሚ ባለሀብቶች ከግል እርሻቸው የሰበሰቡትን ቀይ እሸት እና ጀንፈል ቡና ወደ ቡና ማዘጋጃ እንዱስትሪዎቻቸው ያጓጉዛሉ፤

የወረዳ የቡና ተቆጣጣሪ የታጠበና ያልታጠበ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች ቡና በተገቢው መንገድ ለማዘጋጀት በሚያስችል መልኩ በሰው ኃይል፣ በመሣሪያና በቁሳቁስ ተደራጅተው ለሥራ ዝግጁ መሆናቸውን እንዲሁም የቡና አቅራቢዎች እና ማኅበራት ከመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከላት የገዙት እንዲሁም የቡና አልሚ ባለሀብቶች ከራሳቸው ማሣ የሰበሰቡት የቡና ምርት በትክክል ወደ ቡና ማዘጋጃ እንዱስትሪዎች መድረሱን በማረጋገጥ መረጃ አሰባስቦ በወረዳ ደረጃ ያደራጃል፤

የአቅርቦት ቡና ዝግጅትና ሽኝት

16. የወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት የቡና አቅራቢዎችና ማኅበራት ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የገዙትንና ያዘጋጁትን እንዲሁም አልሚ ባለሀብቶች ያመረቱትንና ያዘጋጁትን ቡና መረጃ በማጠናቀር አቅራቢዎችና ማኅበራት ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት የገዙትን፣ አልሚ ባለሀብቶች ከማሳቸው የሰበሰቡትን የቡና ምርት ወደ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች አስገብተው ካዘጋጁት የቡና መጠን ጋር ያመሳክራል፤

የወረዳ የቡና ጥራትና ግብይት ተቆጣጣሪ የተዘጋጀው ቡና አስፈላጊውን መሥፈርት ማሟላቱን፣ ለቡና መያዣነት በተዘጋጀ ጆንያ መጫኑን፣ ቡናው የሚጫንበት ተሽከርካሪ ቡና ለመጫን ብቁ መሆኑንና ሕጋዊነቱን በማረጋገጥ ቡናውን አሽጎ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ይሸኛል፤ በወረዳው አማካይነት የተሸኘውን ቡና አጠቃላይ መረጃ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ እና ለግብርና ግብይት ዳይሬክቶሬት ያስተላልፋል፤

የወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት አቅራቢ ነጋዴዎች፣ ማኅበራትና አልሚ ባለሀብቶች ቡናቸውን ለማስመርመር ከተፈቀደላቸው የቡና ጥራት ምርመራ ማዕከል ውጭ እንዳያስመረምሩ ተገቢውን ጥንቃቄና ቁጥጥር ያካሄዳል፣

የወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት የሕገወጥ ቡና ዝውውርና የተለያየ ባህርይ ያላቸው ቡናዎች መቀየጥን ለመከላከል አመቺ በሆኑ ቦታዎች ላይ የመቆጣጠሪያ ኬላዎችን በማቋቋም ቁጥጥር ያካሄዳል፣

የወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት አቅራቢው ወይንም ማህበራት ከመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከላት የገዙት ቡና ካዘጋጁት ቡና ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን በድንገተኛ ቆጠራ በማመሳከር ልዩነቱ ሰፊ ሆኖ ከተገኘ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣

ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ከመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከላት ጀምሮ ቡናው ተዘጋጅቶ ለምርመራ እስከሚቀርብ ድረስ ባለው አሠራር ላይ ክትትል በማድረግ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣

የወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት አልሚ ባለሀብቶች በምርት ዘመኑ ሊያገኙ የሚችሉትን የቡና ምርት መጠን በመተመን ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የቡና ጣዕም ምርመራ ማዕከላት አቅርበው ካስመረመሩት የቡና መጠን ጋር ያመሳክራል፣

ከቡና አምራች ዞኖች ቀርቦ የተመረመረና የተሸጠ ቡና መረጃ በዓይነት በማደራጀት ለግብርና ግብይት ዳይሬክቶሬት ይተላለፋል፣

የተሸጠ ቡና መረጃ፣ ለላኪ ድርጅቶችና ለጅምላ ነጋዴዎች ርክክብ የተፈፀመበት ቡና መረጃ በማደራጀት ለግብርና ግብይት ዳይሬክቶሬት ይተላለፋል፣

የዞን ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ከቡና አምራች ወረዳዎች የደረሰውን መረጃ በዞን ደረጃ በማደራጀት ለክልል ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ያስተላልፋል፣

17. የገበክ ማስፋፊክ የሚከተሉት ዋና ዋና የማስፋፊክ □ዴ□ ች አሉት፣

- የትሬድ ፌር ወ□ም ኤግ□ቢሽን ማ□ጋጀትና መሳተፍ፣
- የንግድ ተል□ኮ /Trade Mission/፣
- የንግድ ምልክት (Brand) ሊወ□ላቸው የሚገቡ ምርቶችን በማስመዝገብ ባለቤትነትን ማስከበር፣
- የሕትመትና ማስታወቅያ (ፓምፍሌት፣ ብሮሸርና ፖስተር መጽሔት እና ኦ ቪዥዋል ማ□ጋጀት፣
- በኤምባሲ□ች፣ ሆቴሎችና ታዋቂ ቦታ□ች የሚቀመጥ ናሙና ማ□ጋጀትና መላክ ናቸው::

**የንግድ ትርኢት (Trade Fare/ Exhibition)**

18. የንግድ ትርኢት/ኤግ□ቢሽን በሀገር ውስጥ ማ□ጋጀትና በወጭ ሀገር መሳተፍ የገበክ ማስፋፋት አን□ □ዴ ነው:: በዚህም የገበክ ተዋንክንን በንግድ ትርኢት ወ□ም ኤግ□ቢሽን ላ□ እንዲሳተፉ በማስተባበር ምርቶቻቸውን በውጭ እና በሀገር ውስጥ እንዲክስተዋውቁ የማድረግ ሥራን ያመለክታል:: የንግድ ትርኢት ወ□ም ኤግ□ቢሽን በወረዳ በክልልና በፌዴራል □ረጃ ይዘጋጃል::

**የንግድ ልዑካን ጉብኝት (Trade Mission) ማካሄድ**

19. □ህ ሥራ የሀገሪቱ ምርቶችን በተመረጡ አገሮች ተ□ዋውሮ የማስተዋወቅ፣ እን□ አስ□ላጊነቱም የንግድ ስምምነቶችን የመ□ራረም ተግባራትንና የተለክዩ ምርቶችን የሚገ□ አገራት የንግድ አስ□ጻሚ□ችና ነጋዴ□ችን ወ□ ሀገራችን እንዲመጡና እንዲጎበኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸትን ያካትታል::

**የንግድ ልዑካን የውጭ አገር ጉዞ**

20. የንግድ ልዑካን ተሳታፊዎች የገበክ ማስፋፋት ሥራን እንዲክካሂ□ ወ□ ተመረጡ አገሮች ለመላክ መረጃ□ችን ማሰባሰብ፣ በመረጃው መሠረት የንግድ ልዑካን የሚሄ□በት አገር

የሀገር ምርቶችን ለመግ□ት ባላቸው ፍላጐት ላ□ በመመሥረት መምረጥ፣ የንግድ ተል□ኮ ላ□ የሚሳተፉ አባላት የሚመረጡበትን መስ□ርት ማው□ትና ብ□ታቸውን ማስወሰን፣ በውጭ አገር ለሚካሄ□ው የንግድ ልዑካን ጉብኝት የተመረጡ ተሳታፊ□ች ስለጉዞው እንዲክውቁና አስተክየት እንዲሰጡ የስብሰባ ጥሪ ማድረግ፣ በተል□ኮው ስለሚገኘው ጠቀሜታና የወ□ፊት የንግድ ግንኙነት ከተሳታፊ□ች ጋር በመወክየት እንዲዳብር ማድረግን ያካትታል፡፡ በው□□ት በተ□ረሰው ስምምነት መሠረት የንግድ ተል□ኮ የድርጊት መርሐ-ግብር ማው□ትና የቡድን መሪ መምረጥ፣ ጉብኝት ከሚካሄድበት አገር ኤምባሲ□ች የመግቢክ □ቃድ ለማግኘት አስ□ላጊውን ቅድመ ሁኔታ ለማድረግ ከውጭ ጉዳ□ ሚኒስቴር ጋር በመሆን ሁኔታ□ችን ማመቻቸት፣ ለንግድ ተል□ኮ አስ□ላጊ የሆኑ የቪ□ ሌሎች አስ□ላጊ ሁኔታ□ችን በማመቻቸት፣ የንግድ ተል□ኮ ይካሄዳል፡፡ በንግድ ተልዕኮ ወቅት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን ደግሞ ለገበክ ማስፋፋት የሚጠቅሙ መረጃ□ችን ማሰባሰብ፣ እን□አስ□ላጊነቱ የንግድ ስምምነት መ□ራረም፣ በተል□ኮው የተገኘውን ልምድ አጠናቅሮ ሪፖርት ማድረግና ለገበክ ትስስር ሥራ መጠቀም እንዲቻል ክትትል ማድረግን ያካትታል፡፡

የውጭ አገር የንግድ ልዑካንን መቀበል

21. የውጭ ሀገር ልዑካን ሀገራችንን እንዲጐበኙ ለማስተባበር የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት መካከል መረጃ□ችን ማሰባሰብ፣ የሀገራችንን ምርት ለመግ□ትና ጉብኝት ማድረግ የሚ□ልጉ የውጭ አገር ነጋዴ□ች እና የመንግሥት ተወካዮችን መለየት፣ በጐብኝ□ች ጥክቂና በአገሪቷ ፍላጐት ላ□ በመመስረት ከጐብኝ□ች ጋር ለሚ□ረግ ው□□ት አጀንዳ ማ□ጋጀትና የሚጐበኙ ቦታ□ችን መለየት፣ የንግድ ልዑካንን መቀበልና ው□□ት ማካሄድ፣ እን□አስ□ላጊነቱ ስምምነት መ□ራረም፣ ስምምነት የተ□ረሰባቸውን ነጥቦች መረጃ ለንግ□ ሕብረተሰብና ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት ማሠራጨት፣ ተግባራዊነቱን በመከታተል ሪፖርት ማቅረብና ከተል□ኮ የተገኘውን ልምድ ለቀ□□ ገበክ ትስስር መጠቀም የሚሉትን ያካትታል፣

የንግድ ምልክት ማስመዝገብ፣ ባለቤትነት በማስከበርና ታዋቂ ምርቶችን ገበክ ማስፋፋት፣

22. □ህ ሥራ አገሪቱ ከሌሎች አገሮች ምርት አንፃር ሲታ□ የተለየ ባህር□ና ተ□ላጊነት ክላቸውን ምርቶች በባለቤትነት በማስመዝገብ አስ□ላጊውን ጥቅም እንዲገኝ ማድረግን ክካትታል፡፡ በጥናት ላ□ በመመስረት የንግድ ምልክት ባለቤትነት ማስመዝገብ

የሚክስ□ልጋቸውን ምርቶች/ መለየትና ከሌላው አገር የሚለዩበትን ባህር□ ማወቅ፣ የተለክየ ባሕር□ ክላቸውን ምርቶች ከሌላው ሀገር የሚለዩበትን ባሕር□ /Character/ ከታወቀ በኋላ የምርቶቹን ምልክት /Brand/ አርማ ስክሜ ረቂቅ ማው□ት፣ የምርቶችን የንግድ ምልክቶች አርማና ስክሜ ረቂቅ ላ□ አው□ ጥናት ማ□ጋጀትና ባለድርሻ□ችን ማወክየት፣ በስክሜው ላ□ አው□ ጥናት ከተካሄ□ በኋላ የተገኘውን ሃሳብ ማዳበር፣ በአርማው ስክሜ ላ□ የተመረጡ ምርቶች በተሰ□ቸው ስክሜ እንዲመ□ገቡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ማስ□ጸም፤ የንግድ ምልክት ወ□ም የአርማውን ባለቤትነት ለሚመለከተው ማሳወቅና ማስመዝገብ፣ ምርቶቹ በተለክዩ ስክሜ (Brands) ስም ተገቢ ጥቅምና ዋጋ እንዲክገኙ ክትትል ማድረግ የሚሉትን ያካትታል።

ለገበክ የሚውሉ ምርቶችን በማስሚዲክ በጽሑፍና በድህረ ገጽ ማስተዋወቅ

23. □ህ □ዴ ለገበክ የሚውሉና የማስፋፊክ ሥራ የሚሠራባቸውን የምርት ዓ□ነቶች መለየት ለፓምፍሌት፣ ብሮሽር፣ ፖስተርና ለመጽሔት የሚውልና ለማስሚዲክና በድህረ ገጽ የሚለቀቁ ረቂቅ ጽሑፎችንና ገላጭ ፊልሞችን በው□□ት ለማዳበር አው□ ጥናት ማ□ጋጀት አስተክየት ማሰባሰብና ማዳበር፣ መምረጥ፣ የቀረበውን ረቂቅ ሥራ ከተሰጡ አስተክየቶች አንፃር በቂ መሆኑን ማረጋገጥ፣

24. ሥራ□ቹ በቂ ከሆኑ የገበክ ማስፋፊክ ጽሑፎችን የሚክትሙና የሚክሰራጩ ድርጅቶችን መምረጥ፣ በሕትመት የወጡትን፣ በድህረ ገጽ የተለቀቁትንና በማስታወቂክ የተለቀቁትን የገበክ ማስፋፊክ ጽሑፎችና አጫጭር ፊልሞችን መከታተልና መገምገም። የገበክ ማስፋፊክ □ዴ□ች በየጊ□ው ማሻሻል (updating ) እና ለገበክ ማስፋፊክና ትስስር ተግባር ማዋል የሚሉትን ያካትታል።

ቋሚ ናሙና□ች ማ□ጋጀትና ለገበክ ማስፋፊክ እንዲውሉ ማድረግ

25. ቋሚ የምርት ናሙና□ችን በተመረጡ ወካ□ ቦታ□ች በማስቀመጥ ለገበክ ማስፋፋት የመጠቀም ሥራ የተለክዩ ናሙና□ችን በማሰባሰብ በኤምባሲ□ች፣ በትላልቅ ሆቴሎች፣ በአየር መንገ ችና .... ወ□ተ በመላክ ለገበክ ማስፋፋት ተግባር መዋልን □መለከታል፤

የምርት ገበክ ትስስር የንዑስ ንዑስ የሥራ ሂ□ት

26. በሀገር ውስጥ ገበክ ሊተሳሰሩ የሚችሉ የገበክ ተዋንክንን (አምራቾችን፣ ሰብሳቢ□ችን፣ አግሮ ኢን□ስትሪ□ችን፣ የህብረት ሥራ ላኪ□ች ወ□ተ) በመለየት መረጃውን አጠናቅሮ ሊተሳሰሩ የሚችሉ የገበክ ተዋንክኖችን ፕሮፋ□ል ማ□ጋጀት፣ የተለክየ የመረጃ □ዴ በመጠቀም የትስስር ተዋንክኖችን የፍላጐትና የአቅርቦት መረጃ መሰብሰብ፣ ማጠናቀርና መተንተን፣ የፍላጐትና የአቅርቦት መጠንና ዓ□ነት በአገር ውስጥ ተዋንክን በመለየት ሊተሳሰሩ ለሚችሉት መረጃውን መስጠትና እንዲገናኙ ለማድረግ ሁኔታ□ችን ማመቻቸት፣

የትስስር ተዋንክንን በማገናኘት ለትስስሩ አስ□ላጊውን ድጋፍ በመስጠትና የትስስሩን ሂ□ት በመገምገም መረጃውን ለቀ□□ ሥራ□ች ማሻሻክነት እን□ግብዓትነት እንዲክገለግል መክዝን ያካትታል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በውጭ ገበክ ሊተሳሰሩ የሚችሉ የሀገር ውስጥ ገበክ ተዋንክንን በመለየት፣ ሀገሪቷ ተወዳዳሪ ሆና ልትገባበት የምትችለውን የውጭ ገበክ፣ የምርት ጥራት መስ□ርት መለየት፣ በተለዩት አገሮች ውስጥ ክሉ ገ□ □ችንና የሀገር ውስጥ ላኪ□ችን ፕሮፋ□ል በየጊ□ው በማ□ጋጀት የመረጃ ቋት ውስጥ ማስቀመጥ፣ ከሀገሪቱ የሚቀርበውን ምርት በመጠን፣ ዓ□ነት፣ ጥራትና ላኪ በመለየት ለውጭ አገር ገዥ□ች መስጠትና፣ የምርት ፍላጐት መጠን፣ ዓ□ነትና የጥራት □ረጃ ምርቱን በሚ□ልጉት የውጭ ገ□ □ች ለ□ቶ መረጃውን ለሀገር ውስጥ ላኪ□ች ግንኙነት እንዲክ□ርጉ መስጠትን ያካትታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለተለዩት የውጭ ሀገር ገ□ □ች ናሙና እንዲልኩ ምርቱን ማቅረብ ለሚችሉ የሀገር ውስጥ ላኪ□ች ማሳወቅ፣ የሀገር ውስጥ አቅራቢ□ች፣ ላኪ□ችና የውጭ ገዥ□ች በሚተሳሰሩበት ወቅት አስ□ላጊውን ድጋፍ መስጠትና በትስስር ሂ□ቱ ውስጥ ክጋጠሙትን ችግሮች በመገምገም በቀ□□ ሥራ□ች ማሻሻክ ለማድረግ ን□ግብአትነት እንዲክገለግል መክዝ የሚሉት ዋና ዋና ተግባራት ናቸው፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

## ሀ.ለዓለም ገበያ በሚቀርቡ የግብርና ምርቶች ከምርት ሂደት እስከ ግብይት የሚደረግ የጥራትና የቁጥጥር፣ የክትትልና የድጋፍ ሥርዓት

### ለውጭ ሀገር ገበያ በሚቀርቡ የግብርና ምርቶች ላይ የሚደረግ የጥራት ቁጥጥርን በተመለከተ

27.የንግድ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው የክልል የዞንና የወረዳ አካላት ጋር በመተባበር ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች ተገቢውን የጥራት ደረጃ በማሟላት ሀገሪቱ ከዘርፉ የምታገኘውን ውጤት ለማሳደግ የሚያስችል የተጠናከረ የጥራት ቁጥጥር በየምርቶቹ ባህሪና ዓይነት ከማሳ እስከ ማዕከል ባለው ሰንሰለት ቼክሊስት በማዘጋጀት ወቅታዊ የጥራት ቁጥጥር መደረጉን መከታተልና መደገፍ ይጠበቅበታል፡፡

28.በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት በኦሮሚያ ክልል፣ የጅማ፣ ኢሉባቡር፣ ምስራቅ ወለጋ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች እና በማና፣ ጎማ እና በደሌ ወረዳዎች እንዲሁም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል የሲዳማ፣ ጌዲኦ፣ ቤንች ማጂ እና ሸካ ዞኖች እና በዳሌ፣ ይርጋጨፌ፣ ዬኪ እና ግንቦ ወረዳዎች ውስጥ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የግብርናና የግብይት ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ውጭ ሀገር ገበያ በሚላኩ የግብርና ምርቶችን እንደየምርቶቹ ባህሪና ዓይነት ዝርዝር ዕቅድ አዘጋጅቶ በቼክሊስት መሰረት የጥራት ክትትል የማድረግ ስራ ወደ ዘመናዊ ግብይት በገቡት የምርት ዓይነቶች ማለትም በቡና፣ ሰሊጥና ነጭ ቦለቄ የተሻለ ቢሆንም ወደ ዘመናዊ ግብይት ባልገቡት ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች ማለትም በቅመማ ቅመም፣ የቅባት አህልና በመሳሰሉት ያለው ክትትልና ድጋፍ አነስተኛ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

29.ከዚህ በተጨማሪም በጥራት ክትትሉ ላይ ተጽዕኖ ከሳደሩት ጉዳዮች መካከል በእያንዳንዱ ወረዳ በርካታ ቀበሌዎች ሲኖሩ በእነዚህ ቀበሌዎች ብዛት ያላቸው ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የምርት ዓይነቶች የሚመረቱ ቢሆንም ለየወረዳው የተመደበው የጥራት ቁጥጥር ባለሙያ

አንድ ሰው ብቻ መሆኑ እና በቂ የሎጂስቲክ አቅርቦት አለመኖሩ በወረዳ ውስጥ በሚገኙ በርካታ የሆኑ ቀበሌዎች ላይ እየተዘዋወረ በሚፈለገው ደረጃ የጥራት ቁጥጥሩን ክትትል ለማድረግ እንዳላስቻላቸው ገልፀዋል፡፡

30.የኦዲት ቡድኑ በመስክ ስራ ወቅት በኦሮሚያ ክልልና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ውስጥ የሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከላት እና የአርሶ አደሮች የቡና ማሳ ባካሄደው ስራ በከፋ ዞን ቦንጋ አካባቢ እና በቴፒ ወረዳ የሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ የቡና ግብይት ማዕከላት ያልደረሰ ቡና ወይም ጥቁር ቡና ለገበያ እንደሚቀርብ ለማረጋገጥ ተችሏል፡ በተመሳሳይ መልኩ በሲዳማ ዞን፣ በወንዶ እና ዳሌ ወረዳዎች እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን የማና እና ጎማ ወረዳዎች የሚገኙ ቡና አብቃይ አርሶ አደሮች ቡናን በመኪና መንገድ ላይ አስጥተው የሚያደርቁ መሆናቸውን የኦዲት ቡድኑ ተመልክቷል፡፡

31.ስለጉዳዩ በንግድ ሚኒስቴር የግብርና ምርት ግብይት ዳይሬክቶሬት የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የጥራት ጉዳይ በዋናነት የኤክስተንሽን ተግባር በመሆኑ በግብርና ሚኒስቴር እና በክልሎች ተገቢው ትኩረት በመስጠት በመሰራቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሀገራችን የምርት ጥራት እያደገ እንደሚገኝና በሌላ በኩልም በግብይት ሂደት  ያለውን የምርት ጥራት ለማስጠበቅ በተመረጡ ምርቶች የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀትና ግልጽ ግንዛቤ እንዲያዝበት በማድረግ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ ተገቢው ግብረመልስ እየተሰጠ ጥራት የማስጠበቅ ሥራ በተቀናጀ ሁኔታ እየተከናወነ ስለመሆኑ ሆኖም በተለይ በግብይት ሂደት የሚፈጠረውን የጥራት መጓደል ለማስወገድ በበለጠ ቅንጅት ሊሰራበት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

32.የንግድ ሚኒስቴር ከላይ የተጠቀሰውን ሃሣብ ቢገልጽም ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች ተገቢውን የጥራት ደረጃ እንዲያሟሉ በየምርቶቹ ባህሪና ዓይነት ከማሳ እስከ ማዕከል ባለው ሰንሰለት ቼክሊስት በማዘጋጀት የተጠናከረ ወቅታዊ የጥራት ክትትል በየደረጃው በሚገኙ አካላት በተለይ ወደ ዘመናዊ ግብይት ባልገቡ ምርቶች አለመጠናከሩ፣ በየወረዳዎቹ የተመደቡት የጥራት ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ቁጥር በቂ አለመሆኑና ለስራቸው የሚያስፈልጋቸው የሎጂስትክ አቅርቦት አለመሟላቱ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል በሚገኙ አንዳንድ ወረዳዎች ያልደረሰ ቡና ወይም ጥቁር ቡና ለገበያ መቅረቡ እንዲሁም በሁለቱ ክልሎች በሚገኙ አንዳንድ ወረዳዎች የሚገኙ የቡና

አምራች አርሶ አደሮች ቡናን በመኪና መንገድ ላይ አስጥተው የሚያደርቁ መሆኑ ሀገሪቱ ለውጭ ሀገር ገበያ የምታቀርባቸው የግብርና ምርቶች በጥራት ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ እና በዘርፉ ልታገኝ የሚገባትን የተሻለ የውጭ ምንዛሪ እንዳታገኝ ሊያደርጋት ይችላል፡፡

## የግብይት አዋጅና ደንብ ያልወጣላቸው ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች የግብይት ስርዓትን በተመለከተ

33.የንግድ ሚኒስቴር የግብይት አዋጅና ደንብ ያልወጣላቸው ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች የግብይት አዋጅ እና ደንብ እንዲወጣላቸው ሊያደርግ እና ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር ምርቶቹ በሚመረቱበት አካባቢ የመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከላት እንዲገነቡ እና ተገቢውን የጥራት ደረጃ እንዲያሟሉ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

34.በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት በኦሮሚያ ክልል የኢሉባቡር፣ ጅማ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ ዞኖች እና በማና፣ ጎማ፣ ደበና ወረዳዎች እንዲሁም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል የከፋ፣ ሲዳማ እና ጌዲኦ ዞኖች፣ በዳሌ፣ ይርጋጨፌ፣ ዱኪ፣ ግንቦ ወረዳዎች በሚገኙ የንግድና ገበያ ልማት ቢሮዎች የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ወደ ዘመናዊ የግብይት ስርዓት የገቡና አዋጅና ደንብ የወጣላቸው የቡና፣ ሰሊጥ እና ነጭ ቦሎቄ የምርት ዓይነቶች ብቻ ሲሆኑ ሌሎች ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች ማለትም ለቅመማ ቅመም፣ የቅባት እህሎች ቀይ ቦለቄና የመሳሰሉት የግብይት አዋጅና ደንብ እስካሁን እንዳልተዘጋጀላቸው እና ምርቶቹ በሚመረቱበት አካባቢም የመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከላት እንዳልተገነባላቸው ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የምርቶቹን ጥራትና የግብይት ስርዓት በዘመናዊ አሠራር ለመደገፍ የሚያስችል ሁኔታ እንዳልተዘረጋ ገልፀዋል፡፡

35.በተመሳሰይ መልኩ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመረጠው ቃለ-መጠይቅ ከቀረበላቸው፣ በመጠይቅ (survey question) እና በፊት ለፊት ውይይት (focus group discussion) በተሰበሰበው መረጃ መሰረት ለሌሎች ለውጪ ገበያ ለሚቀርቡ የግብርና ምርቶች የግብይት አዋጅና ደንብ እንዳልወጣላቸውና ምርቶቹ በሚመረቱበት አካባቢ የመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከላት እንዳልተገነባላቸው ገልጸዋል፡፡

36.ስለጉዳዩ የንግድ ሚኒስቴር የግብርና ምርት ግብይት ዳይሬክቶሬት የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ግብይት በዋናነት የሚፈጸመው በንግድ ህጉ እና ለየምርቶቹ በተናጠል በተዘጋጀው የግብይት ህጎች መሠረት ስለመሆኑና የተለየ ሁኔታ ሲያስፈልግ እንደ ምርቶቹ ባህሪ እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ የህግ ማዕቀቀፍ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንደሚደረግ በመሆኑም በዋናነት ለኤክስፖርት ለሚውሉ የቡና፣ ሰሊጥና ነጭ ቦሎቄ ምርቶች የህግ ማዕቀፍ በማጋጀት ዘመናዊ ግብይት እየተፈፀመ ስለመሆኑ በቀጣይም ስንዴንና በቆሎ ምርቶች ላይ ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ለወደፊትም በፌዴራልና በክልሎች በቅንጅት ጥናት በማድረግ ለሌሎችም በተመሳሳይ እንደሚከናወን ገለጸዋል፡፡

37.አንዳንድ ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች የግብይት አዋጅና ደንብ ያልወጣላቸው መሆኑ እና ምርቶቹ በሚመረቱበት አካባቢ የመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት አለመገንባቱ ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች በጥራት ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ እና ሀገሪቱ ከዘርፉ የምታገኘውን የውጭ ምንዛሪ እንዳታገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ወደ ውጭ የሚላኩ የግብርና ምርቶች ላይ

## ስለሚሰሩ የጥራትና ደረጃ ማዕከላትን በተመለከተ፡-

38.የንግድ ሚኒስቴር ወደ ውጭ ሀገር ገበያ የሚላኩ የግብርና ምርቶችን ጥራት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ የጥራትና ደረጃ ማዕከላት ምርቶቹ በሚመረቱባቸው አካባቢዎች እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ በማድረግ የማዕከላቱን ውጤታማነት መከታተል ይጠበቅበታል፡፡

39.በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት በኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ምስራቅ ወለጋ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች እና ማና፣ ጎማ፣ በደሌ ወረዳዎች እንዲሁም በደቡብ ክልል የሲዳማ፣ ጌዲኦ፣ ቤንች ማጂ እና ሻካ ዞኖች ዳሌ፣ ይርጋጨፌ፣ ዬኪ፣ ግንቦ ወረዳዎች ውስጥ ከሚገኙ የግብርና ቢሮዎችና የግብይትና ሕብረት ሥራ ኤጀንሲ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ-መጠይቅ የጥራትና ደረጃ ማዕከላት ምርቶች በሚመረቱበት አካባቢ እየተቋቋሙ ቢሆንም ወደ ውጪ ከሚላኩት የግብርና ምርቶች ብዛትና አይነት አንጻር በቂ አለመሆናቸውን እና ማዕከላቱም መመሪያው በሚያዘው መሰረት እየተገነቡ እንዳልሆኑ ገልጸዋል፡፡ የተገነቡት የግብይት ማዕከላትም ወደ ዘመናዊ የግብይት ማዕቀፍ ለተካቱት ምርቶች ብቻ መሆናቸውን እና ወደ ዘመናዊ የግብይት ማዕከላት የልተካታቱት የግብርና ምርቶች በእነዚህ የጥራትና ደረጃ ማዕከላት የጥራት ሥራ የማይሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

40. ስለጉዳዩ የንግድ ሚኒስቴር የግብርና ምርት ግብይት ዳይሬክቶሬት የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ጥራት የሚጀምረው ከአርሶ አደሩ በመሆኑ ግብርና ሚኒስቴርና ክለሎች ምርት ጥራቱን እንዲጠብቅ የማድረግ ተግባር እያከናወኑ እንደሚገኝ ሆኖም ምርቱ ወደ ገበያ ሲወጣ ጀምሮ ባለው ሂደት የምርቱን ጥራት ለማሰጠበቅ ንግድ ሚኒስቴር ከሌሎች ባለድርሻ አካላት እየተሰራበት እንደሚገኝ ለእዚህም ለተመረጡ ምርቶች ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን የጥራት ማስጠበቂያ ማዕከላት ማቋቋሙን ተግባሩ እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡

41.የጥራትና ደረጃ ማዕከላት ወደ ውጭ ገበያ በሚቀርቡ በሁሉም  የግብርና የምርት አይነቶች እና የግብርና ምርቶቹ በሚመረቱበት በቅርብ አካባቢ እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ ባለመደረጋቸው ወደ ውጭ በሚላኩ ምርቶች በጥራት ተመርተው ወደ ገበያ እንዲቀረቡ ለማድረግ አያስችልም፡፡

<u>የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት ወደ ውጭ ገበያ የሚላኩ</u>

<u>የግብርና ምርቶችን ለሚያመርቱ አርሶ አደሮች እና የግብርና</u>

<u>ባለሙያዎች የሚሰጠውን የጥራት ግብረ መልስ አሠራር በተመለከተ</u>

42.ለንግድ ሚኒስቴር ተጠሪ ከሆኑት መስሪያ ቤቶች አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት ወደ ውጭ ሀገር ገበያ የሚላኩ የግብርና ምርቶች ላይ የሚታዩ የጥራት ችግሮች እንዲሻሻሉ በግብይት ስርዓቱ የቀረበው ምርት ያገኘውን ደረጃ እና ምርቱ ያለበትን የጥራት ችግሮች እንዲያሻሻሉ ለአምራች አርሶ አደሮችና ለግብርና ባለሙያዎች የሚደርስበት የግብረ መልስ (feed back) ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የንግድ ሚኒስቴርም ይህ ስርዓት ሥራ ላይ ስለመዋሉ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

43.በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ የጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ምስራቅ ወለጋ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች እና በማና፣ ጎማ፣ በደሌ ወረዳዎች እንዲሁም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ስር ከሚገኙ ሲዳማ፣ ጌዲኦ፣ ቤንች ማጂ እና ማሻ ዞኖች እና የዳሌ፣ ያኪ እና ይርጋጨፌ ወረዳዎች የግብይትና ህብረት ሥራ ቢሮ ስራ ኃላፊዎች ጋር የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው ቃለ-መጠይቅ ወደ ውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች በጥራት እንዲመረቱ ከማስቻል አንጻር አርሶ አደሮች ያመረቱት ምርት ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ካቀረቡ በኂላ ለምርቱ የተሰጠው ደረጃና በጥራቱ ላይ የታዩ

የጉድለት መረጃዎች ለግብርና ባለሙያዎች እና ለአምራች አርሶ አደሮች እንደማይደርስ ገልጸዋል፡፡ ይህም በመሆኑ በምርቶቹ ላይ የታዩ የጥራት ጉድለቶች ተለይተው በጥራቱ ላይ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ እንዳላስቻላቸው ገልጸዋል፡፡

44.ስለጉዳዩ በንግድ ሚኒስቴር የግብርና ምርት ግብይት ዳይሬክቶሬት የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው ጥራትን በአካባቢው በሚገኘው መረጃ ተመስርቶ ማከከናወን የሚያስችል ሁኔታ እንዳለ በመጥቀስ ሆኖም ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚቀርበውን ምርት የጥራት ደረጃና የጥራት ጉድለትን ማወቅ ተጨማሪ ድጋፍ እንደሚኖረው ስለሚታመንበት ግብረ መልስ የሚገኝበት ሥርዓት በተወሰኑ አካባቢዎች እንዲዘረጋ እየተደረገ ሲሆን ይኸው እንዲሰፋና ለወደፊትም ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

45.የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለውጭ ሀገር ገበያ በአቅራቢዎች የሚቀርበው የግብርና ምርት ያገኘውን ደረጃና በጥራቱ ላይ የታዩ ጉድለቶች እንዲሻሻሉ ለማስቻል ግብረ መልስ (feed back) ለግብርና ባለሙያዎች እና ለአርሶ አደሮች እንዲደርሳቸው አለመደረጉ ችግሩን በቀጣይ የምርት ሂደት በማሻሻል ጥራት ያለው ምርት ለውጭ ሀገር ገበያ ለማቅረብ አያስችልም፡፡

<u>ወደ ውጭ ሀገር በሚላኩ የግብርና</u>

<u>ምርቶች የግብይት ሥርዓት ችግሮች ላይ</u>

<u>የሚካሄደውን ስራ በተመለከተ፣</u>

46.ለንግድ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆነው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት ለውጭ ሀገር ገበያ የግብርና ምርቶችን ለሚልኩ ላኪዎች በሚያቀርቧቸው ምርቶች ላይ በገባው ውል በተገለጸው የጥራት ደረጃና መጠን መሰረት ሊያቀርብ እና የግብርና ምርቶችም ዋጋ የዓለም የገበያ ሁኔታን ያገናዘበ እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጡም ኢኮኖሚያዊና ቀልጣፋ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የንግድ ሚኒስቴርም የተዘረጋው የግብይት ስርዓት ላኪዎችን እንዲያበረታታ እና ችግሮች ሲያጋጥሙም በወቅቱ እንዲፈቱ ለማስቻል አሰፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

47. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ቃለ-መጠይቅ ከተደረገላቸው 12 የግብርና ምርት ወደ ውጭ ሀገር የሚልኩ ላኪዎች (exporters)፣ በመጠይቅ (survey questionnaire) አስተያየታቸውን ከገለጹ 18 ላኪዎች እና በፊት ለፊት ውይይት (focus group

discussion) ከተሳተፉ ላኪዎች ተሰብስቦ በተተነተነው መረጃ መሰረት ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚገዙት ምርት የኪሎ ጉድለት እንደሚያሳይ እንዲሁም ምርቱ በተገዛው የጥራት ደረጃ ልክ እንደማይደርሳቸው ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኢትጵያ ምርት ገበያ የግብርና ምርቶች የመገበያያ ዋጋ ከዓለም የገበያ ዋጋ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ላኪዎች በውጭ ሀገር ገበያ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ እንዳደረጋቸው ገልጸዋል፡፡ በአገልግሎት አሰጣጥ በኩልም በተለይ ሁመራ በሚገኘው የስሊጥና ነጭ በሎቄ መጋዘን ያለው የአገልግሎት አስጣጥ ቀልጣፋ ባለመሆኑ ምርቱን ለመጫን ከአስራ አምስት ቀናት በላይ ተሽከርካሪዎች ያለሥራ የሚቆሙ በመሆኑ ለአላስፈላጊ ወጪ እየዳረጋቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

48.ስለጉዳዩ በንግድ ሚኒስቴር የግብርና ምርት ግብይት ዳይሬክቶሬት የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ እንደጀማሪ የታየበት ክፍተት የሚጋነን ባይሆንም በኮንትራቱ መሠረት በጥራት ያለማስረከብ ችግርን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል ተግባር ምርት ገበያው ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ጋር በመተባበር እየተሰራበት እንደሚገኝና ሚኒሰቴር መስሪያቤታችንም በሚካሄደው የክትትልና ድጋፍ ሥራ የሚያገኛቸው ማረጃዎችን ግብረ መልስ በመስጠት ተገቢው ድጋፍ እየተደረገና ችግሩም እየተፈታ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

49.የንግድ ሚኒስቴር ከላይ የተጠቀሰውን ሃሣብ ቢገልጽም የግብርና ምርት ላኪዎች (exporters) ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚገዙት ምርት የኪሎ ጉድለት የሚያሳይ መሆኑ፣ በተገዛው የጥራት ደረጃ ልክ የማይደርሳቸው መሆኑ እና የኢትጵያ ምርት ገበያ የግብርና ምርቶች የመገበያያ ዋጋ ከዓለም የገበያ ዋጋ ጋር የማይጣጣም መሆኑ እንዲሁም የመጋዘን አገልግሎት አስጣጥ ቀልጣፋ አለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት የተሰበሰቡ መረጃዎች የሚያስረዱ በመሆናቸው ላኪዎች(exporters) በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ እና በዘላቂነት (sustainably) እንዳይቀጥሉ በማድረግ በግብርና ምርት የውጭ ግብይት የሚጠበቀውን ውጤት እንዲያመጣ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ሰ.ወደ ውጭ ሀገር ገበያ ሊላኩ ለሚችሉ የግብርና ምርቶች ገበያ የማፈላለግ ሥርዓት

### ወደ ዘመናዊ የግብይት ስርዓት ያልገቡ የግብርና ምርቶች አዲስ ገበያ ማፈላለግን በተመለከተ

50.የንግድ ሚኒስቴር ወደ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት ያልገቡ እና በውጭ ሀገር ገበያዎች ተፈላጊነት ያላቸውን የግብርና ምርቶች በመለየት፣ ተቀባይ ሊሆኑ የሚችሉ ሀገራት (potentional market) በማጥናት ለግብይት የሚፈለገውን የግብርና ምርት የጥራት ደረጃ እና መጠንን የሚገልጽ መረጃዎችን ምርቶቹ ሊመረቱባቸው ለሚችሉ የክልል፣ የዞን እና የወረዳ ግብርናና የንግድ ቢሮዎች እንዲሁም ለላኪዎች በማድረስ የምርትና የግብይት ሥርዓቱን ማስፋፋትና ማጠናከር ይጠበቅበታል፡፡

51.በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በመስክ ስራ ከታዩት በኦሮሚያ ክልል የጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ምስራቅ ወለጋ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች እና በማና ፣ ጎማ፣ በደሌ ወረዳዎች እንዲሁም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ወስጥ ከሚገኙ ሲዳማ፣ ጌዲኦ፣ ቤንች ማጂ እና ማሻ ዞኖች እና የዳሌ፣ ዬኪ እና ይርጋጨፌ ወረዳዎች ውስጥ ከሚገኙ የግብርናና የንግድ ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃል-መጠይቅ በውጭ ሀገራት ገበያዎች ቢቀርቡ የተሻለ ውጤት ሊያስገኙ የሚችሉ የግብርና ምርት ዓይነት እና መጠን የሚገልጽ መረጃ በንግድ ሚኒስቴር በኩል ተጠናክሮ እንደማይተላለፍላቸው ገልጸዋል፡፡ በተለይ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል የግብይት እና ህብረት ስራ ኤጀንስ የስራ ኃላፊ ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው እንደገለጹት በክልሉ ውስጥ የካሳቫና የዝንጅብል ምርት በስፋት እንደሚመረት እና የውጭ ገበያ የማፈላለግ ሥራ ባለመሰራቱና ተቀባይ ሀገራት የሚጠቁም መረጃ በንግድ ሚኒስቴር ባለመቅረቡ ምርቶቹ ለብክነት እየተዳረጉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን የቅመማ ቅመም ምርት የሚመረት ቢሆንም የውጭ ገበያ የማፈላለግ ሥራ አለመሰራቱ እና ተቀባይ ሀገራትን ፍላጎት የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ባለመቅረቡ አርሶአደሩ ምርቱን ትኩረት ሰጥቶ እንዲያስፋፋ አለመደረጉን እና ብዙ ያልተሰራበት ነገር ግን ትኩረት ቢሰጠው ከፍተኛ ውጤት ሊያስገኝ የሚያችል አቅም መኖሩን ገልጸዋል፡፡

52.ከዚሁ ጋር በተያያዘ በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ስለጉዳዩ ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ላኪዎች፣ በመጠይቅ (survey questionnaire) ከተካተቱ 18 ላኪዎች እና በፊት ለፊት ውይይት (focus group discussion) ተጋብዘው ከተወያዩ ላኪዎች ተሰብስቦ ከተተነተነ መረጃ ለማወቅ እንደተቻለው በውጭ ሀገራት ተፈላጊ የሆኑ የግብርና ምርቶችን የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ በንግድ ሚኒስቴር በኩል በተጠናከረ ሁኔታ ተዘጋጅቶ እንደማይቀርብላቸው ተረጋግጧል፡፡

53.ስለጉዳዩ በንግድ ሚኒስቴር የግብርና ምርት ግብይት ዳይሬክቶሬት የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ግብርና ሚኒስቴር ለስፔሻላይዜሽንና ለዳይቨርሲፊኬሽን የሚረዱ በርካታ ሰነዶች በማውጣት እንዲሰራጩ ያደረገ ሲሆን ንግድ ሚኒስቴርም የገበያ አዝማማያን እያየ መረጃ እየሰጠ እንደሚገኝ በተለይ ዝንጅብልን በተመለከተ የዓለም ገበያ መዋዥቅ በተለይ ምርት ከተመረተ በኋላ በየጊዜው እንደሚያጋጥምና ይህንኑም ለክልሎች በጊዜው መረጃ እንደሚሰጣቸውና ሆኖም ካሳቫ እስካሁን በውጪ ገበያ ስለመፈለጉ መረጃ ባለመኖሩ በአገር ውስጥ ግብይት እንደሚደረግበት ገልጸዋል፡፡

54.የንግድ ሚኒስቴር ከላይ የተጠቀሰውን ሃሣብ ቢገልጽም ወደ ዘመናዊ የግብይት ስርዓት ያልገቡና በውጭ ሀገራት ገበያዎች የሚፈለጉ የግብርና ምርት አይነቶችን በማጥናት መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመተንተንና በማጠናከር ምርቶቹ ሊመረቱባቸው ለሚችሉ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች የግብርናና የግብይት ቢሮዎች እንዲሁም ለላኪዎች እንዲደርሳቸው አለመደረጉን ከክልሎች በተሰበሰበው መረጃ የታወቀ በመሆኑ በሀገራችን ተመርተው በውጭ ሀገራት ገበያዎች ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ማምጣት የሚችሉ ምርቶችን በስፋት እንዳይመረቱ እና ከዘርፉ የሚጠበቀውን የተፋጠነ እድገት እና ውጤታማነት እንዳይገኝ የጎላ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

## ወደ ውጭ ገበያ የሚቀርቡ ዋና ዋና የግብርና ምርቶችን አስመልክቶ የገበያ ፍላጎት እና የዋጋ ትንቢያ መካሄዱን በተመለከተ፣

55.የንግድ ሚኒስቴር ወደ ውጭ ሀገር ገበያ የሚላኩ ዋና ዋና የግብርና ምርቶችን የገበያ ፍላጎት እና የዋጋ ትንቢያ ጥናት ሊያካሄድ እና ውጤቱንም ለላኪዎችና ለሚመለከታቸው አካላት ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

56.በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በመስክ ስራ ከታዩት በኦሮሚያ ክልል የጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ምስራቅ ወለጋ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች እና በማና፣ ጎማ፣ በደሌ ወረዳዎች እንዲሁም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ወስጥ ከሚገኙ ሲዳማ፣ ጌዲኦ፣ ቤንች ማጂ እና ማሻ ዞኖች እና የዳሌ፣ ዬኪ እና ይርጋጨፌ ወረዳዎች ውስጥ ከሚገኙ የግብርናና የንግድ ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃል-መጠይቅ ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ የግብርና ምርቶችን በተመለከተ በንግድ ሚኒስቴር የገበያ ፍላጎትና የዋጋ ትንበያን አስመልክቶ የተጠና ጥናት እንዳልደረሳቸው ገልጸዋል፡፡

57.በተመሳሳይ መልኩ በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው 12 ላኪዎች፣ በመጠይቅ (survey questionaire) ከተላከላቸው 18 ላኪዎች እና በፊት ለፊት ውይይት (focus group discussion) ከተሳተፉ 17 ላኪዎች በተሰበሰበው መረጃ ወደ ውጭ ሀገር ገበያ የሚላኩ ዋና ዋና የግብርና ምርቶችን አስመልክቶ የገበያ ፍላጎት እና የዋጋ ትንቢያ ጥናት በንግድ ሚኒስቴር እንዳልተካሄደና በሀገሪቱም የዋጋ ትንቢያ እንደማይደረግ ጉዳዩን በተመለከተ ምንም ዓይነት መረጃ ከንግድ ሚኒስቴር እንዳልደረሳቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

58.ስለጉዳዩ በንግድ ሚኒስቴር የግብርና ምርት ግብይት ዳይሬክቶሬት የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የ"FOB" ዋጋን ተጨምሮ ከተለያ ምንጮች የሚገኙ መረጃዎች ለክልሎችና ለገበያ ተዋንያኖች በተለይም በዘርፍ ማህበራቸው በኩል እንዲደርሳቸው እየተደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

59.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከላይ የተጠቀሰውን ሃሣብ ይገለጽ እንጂ ወደ ውጭ ሀገር ገበያ የሚላኩ ዋና ዋና የግብርና ምርቶችን አስመልክቶ የገበያ ፍላጎትና የዋጋ ትንበያ ጥናት በንግድ ሚኒስቴር አለመካሄዱ ሀገሪቱ በዓለም ገበያ ተፈላጊና የተሻለ ዋጋ ሊያስገኝ የሚያስችል ምርቶችን በማቅረብ ተወዳዳሪ እንዳትሆን ያደርጋታል፡፡

## ሐ. የንግድ ሚኒስቴር የመረጃ አያያዝና ስርጭት ስርዓት

### የግብርና ምርቶች የውጭ ሀገር ግብይት በዘመናዊ

### የመረጃ ስርዓት መደገፋን በተመለከተ:

60.የንግድ ሚኒስቴር በግብርና ምርቶች የውጭ ግብይት ለተሰማሩ አካላት የተሻለ ተወዳዳሪ እና ውጤታማ ሊያደርጋቸው የሚችል በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ባለሙያ የተደራጀ የመረጃ አያያዝ ስርዓት በመዘርጋት ለዘርፉ የሚያስፈልጉትን የዓለም አቀፍ

መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመተንተንና በማጠናከር ለላኪዎች፣ በምርት ሂደት እና በግብይት ስርዓቱ ለሚሣተፉ አካላት ፈጣንና ወቅታዊ መረጃ ሊያሠራጭ እና ለዘርፉ የመረጃ ቋት (data base) ማዕከል በመሆን ማገልገል ይጠበቅበታል፡፡

61.በኦዲት ወቅት በንግድ ሚኒስቴር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ፣ በተካሄደ የመረጃ ክለሳ እና በግብርና ምርቶች የውጭ ሀገር ግብይት እና የምርት ሂደት ተሳታፊ ከሆኑ የተለያዩ አካላት በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የንግድ ሚኒስቴር የመረጃ አያያዝ ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ ያልተደራጀና በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት የሚያቀርባቸው መረጃዎች ውስን መሆናቸውን እና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ለዘርፉ ሀገር አቀፍ የመረጃ ቋት ማዕከል በመሆን እያገለገለ እንደማይገኝ ታውቋል፡፡

62.በናሙና ተመርጠው ቃለ-መጠይቅ ከተደረገላቸው 12 ላኪዎች፣ በመጠይቅ (survey questionnaire) መረጃ ከተሰበሰበባቸው 18 ላኪዎች እና በፊት ለፊት ውይይት (focus group discussion) ተሳታፊ ከሆኑ 17 ላኪዎች ከተሰበሰበው መረጃ ንግድ ሚኒስቴር የአለም አቀፍ የገበያ መረጃን በመሰብሰብ፣ በመተንተንና በማጠናከር በውጭ ንግዱ የተሻለ ተወዳዳሪ እና ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል መረጃ አንደማያስተላልፍላቸው ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም በስራ ሂደት የሚያስፈልጋቸውን ወሳኝ መረጃዎች እጥረት ለመፍታት በተበታተነ ሁኔታ መረጃዎችን ከድህረ-ገጽ እያፈላለጉ እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡

63.ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት በኦሮሚያ ክልል የጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ምስራቅ ወለጋ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች እና በማና፣ ጎማ፣ በደሌ ወረዳዎች እንዲሁም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ወስጥ ከሚገኙ ሲዳማ፣ ጌዲኦ፣ ቤንች ማጂ እና ሸካ ዞኖች እና የዳሌ፣ ዬኪ፣ የይርጋጨፌ እና ግንቦ ወረዳዎች ውስጥ ከሚገኙ የግብርናና የንግድ ቢሮ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃል-መጠይቅ የንግድ ሚኒስቴር የግብርና ምርቶች የውጭ ግብይት በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችሉ ወሳኝ የአለም አቀፍ የግብይት መረጃዎችን በማጠናከር የማያቀርብላቸው በመሆኑ አርሶ አደሮች በተለምዶ ምርቶችን እያመረቱ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

64.ስለጉዳዩ በንግድ ሚኒስቴር የግብርና ምርት ግብይት ዳይሬክቶሬት የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ መረጃ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅት የሚሰራ በመሆኑ ይኸው እየተተገበረ እንደሚገኝና በዚሁ መሠረት ወደ ዘመናዊ ግብይት የገቡ ምርቶች የዋጋ፣ አቅርቦትና ፍላጎት መረጃ ከኢትየጵያ ምርት ገበያ፣ የምርት አቅርቦት መረጃ በኢትዮጵያ

ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን፣ የኤክስፖርት መረጃ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ አርሶ አደሩ የመሸጫ ዋጋ በኢትዮጵያ አህል ንግድ ድርጅት እና የደንበኞች ፍላጎት በኢፌዴሪ ኤምባሲዎች ምንጭነት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የመረጃ ክፍል አማካኝነት እየተሰራጨ እንደሚገኝና ጥረቱን በማጠናከር መቀጠል እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

65.ይሁን እንጂ ስለጉዳዩ ንግድ ሚኒስቴር የሰጠው መልስ የሌሎች ባለድርሻ አካላት ኃላፊነት የሚመለከት እንጂ የራሱን ኃላፊነት በሚመለከት ስለተነሱት ጉዳዮች በቂ መልስ ያልተሰጠበት በመሆኑ በተለይ የንግድ ሚኒስቴር በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ባለሙያ የተደራጀ ለግብርና ምርቶች የውጭ ግብይት ወሳኝ የሆኑ የአለም አቀፍ መረጃዎችን በመሰብሰብና በማጠናከር በዘርፉ በግብይት እና በምርት ሂደት ለተሰማሩ አካላት ወቅታዊ መረጃ አለማቅረቡና ለዘርፉ አገር አቀፍ የመረጃ ቋት ማዕከል በመሆን አለማገልገሉ ሀገሪቱ በዘርፉ በጥራት እና በዋጋ ተወዳዳሪ በመሆን ልታገኝ የምትችለውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እንዳታገኝና በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ውጤታማነት እና የስራ ዘላቂነት (sustainability) ላይ የጎላ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

## መ. <u>የውጭ ንግድ ማስፋፋያ ጉዳይ በሚመለከታቸው አካላት መካከል ያለው ቅንጅታዊ አሰራር፣</u>

### <u>የንግድ ሚኒስቴር ከክልል የኤክስፖርት ድጋፍ ኮሚቴዎች ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በተመለከተ፡</u>

66.የንግድ ሚኒስቴር በክልል ከተደራጁ የኤክስፖርት ልማት ድጋፍ ኮሚቴዎች ጋር በአፈጻጸም ሂደት ዙሪያ የጋራ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት በሥራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች በወቅቱ እንዲፈቱ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

67.በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩና ቃለ-መጠይቅ ከቀረበላቸው የኦሮሚያ ክልል የንግድና ግብይት ቢሮ እና የደቡብ ክልል የግብይትና ህብረት ሥራ ኤጀንሲ የሥራ ኃላፊዎች እንደገለጹት የኤክስፖርት ልማት ድጋፍ ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ የተደረገ ቢሆንም ኮሚቴዎቹ ከተቋቋሙ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን የኤክስፖርት ልማቱን ለመደገፍ ከንግድ ሚኒስቴር ጋር በየወቅቱ የጋራ ውይይት በማካሄድ በሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት የተጠናከረ ሥራ እንዳልተሰራ ገልጸዋል፡፡ ስራው ያልተከናወነበትን

ምክንያት ሲገልጹ የኮሚቴው አባላት ከተለያዩ መ/ቤቶች የተወጣጡ በመሆኑ ሥራውን እንደራስ ስራ አድርጐ ያለማየት ችግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

68.ስለጉዳዩ የንግድ ሚኒስቴር የግብርና ምርት ግብይት ዳይሬክቶሬት የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የጋራ መድረኩ በዋና ዋና ምርቶች በተከታታይ እየተደረገ እንደሚገኝና በተጨማሪም ተከታታይ የባለሙያዎችና አመራሩ የመስክ ክትትልና ድጋፍም ጭምር ውይይት እንደሚደረግና ተገቢው ግንኙነት እየተደረገ በመሆኑ ችግር ያለመሆኑን እንዲሁም በክልል የኤክስፖርት ምርቶች ለመከታተል በተለይ ለቡና፣ ለሌጥና ነጭ ቦሎቄ ግብረ ኃይሎች በየደረጃው ተቋቁመው ከሚኒስቴር መስሪያቤቱ ጋር በቅንጅት እየተሠሩ እንደሚገኙ ነገር ግን ወጥነት ባለው መልክ በክልል ኤክስፖርት ልማት ድጋፍ ኮሚቴ ለመደገፍ ኮሚቴው እየተደራጀ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

69.የንግድ ሚኒስቴር በየክልሉ ባሉ የውጪ ንግድ ድጋፍ ኮሚቴዎች ጋር ወቅታዊ የውይይት መድረክ አለማዘጋጀቱ በውጭ ንግድ የሚከሰቱ የአፈጻጸም ችግሮችን ለይቶ ለመቅረፍ አያስችልም፡፡

## <u>የግብርና ምርቶች የውጭ ንግድን በጥራት ለማቅረብ የሚያግዝ የጆኒያ እና የፒፒ ከረጢት ለአምራቾች ማቅረብን በተመለከተ፤</u>

70.የንግድ ሚኒስቴር ለውጭ ንግድ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን በጥራት ለማቅረብ የሚያግዙ ደረጃቸውን የጠበቁ በቂ የጆኒያ፣ የፒፒ ከረጢት እና የቡና ማስጫ አልጋ ለመሥራት የሚያገለግል ሽቦ ለአርሶ አደሮች በተመጣጣኝ ዋጋ ከአቅራቢዎች እንዲያገኙ ከጆኒያና ፒፒ ከረጥት አምራች ድርጅቶች ጋር የማቀናጀትና የማስተሳሰር ሥራ ሊሰራ ይገባል፤

71.በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት በኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ምስራቅ ወለጋ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች እንዲሁም በደቡብ ክልል ሲዳማ፣ ጌዲኦ ፣ቤንች ማጂ እና ማሻ ዞኖች ውስጥ ከሚገኙ ጉዳዩ ከሚመለከተቸው የግብርና ቢሮ፣ የግብይት እና ህብረት ሥራ ኤጀንሲ የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ-መጠይቅ ባለፈው የምርት ዘመን የጆኒያ፣ ፒፒ ከረጥት እና የቡና ማስጫ አልጋ ለመስራት የሚያገለግል ሽቦ እጥረት እንደነበረባቸው ገልጸዋል፡፡

72.ስለጉዳዩ የንግድ ሚኒስቴር የግብርና ምርት ግብይት ዳይሬክቶሬት የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ችግር በገጠማቸው ግብዓቶች ለምሳሌም በጆንያ አቅርቦት፣ በኮንቴርና ትራንስፖት ተገቢው የማስተሳሰር ሥራ በመስራት ችግሩ እንደተፈታ በቀጣይም በዕቅድ በመያዝ እየተሰራበት እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

73. የንግድ ሚኒስቴር የስራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ ችግሩ እንደተፈታ ይግለጹ እንጂ ችግሩ መፈታቱን የሚያሳይ ተጨባጭ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ አላቀረቡም በመሆኑም ይህ ሁኔታ የንግድ ሚኒስቴር ለውጭ ንግድ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን በጥራት ለማቅረብ የሚያግዙ የጆኒያ፣ ፒፒ ከረጢት እና የቡና ማስጫ አልጋ ለመስራት የሚያገለግል ሽቦ አቅራቢዎችን በማስተባበር አርሶአደሮች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ አለማድረጉ እና እጥረት መከሰቱ ለውጭ ንግድ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች በተፈለገው ጥራት እንዳይቀርቡ በማድረግ ዘርፉ በዓለም ገበያ የሚኖረውን ተወዳዳሪነት ላይ የጎላ ተጽዕኖ ያስከትላል፡፡

## <u>ወደ ውጭ ሀገር ገበያ የሚላኩ የግብርና ምርቶች</u>

## <u>የህገ-ወጥ ግብይት ቁጥጥርን በተመለከተ፣</u>

74. የንግድ ሚኒስቴር ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች በዘመናዊና ህጋዊ የግብይት ሥርዓት ውስጥ ገብተው የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ በማሟላት እንዲቀርቡ ለማስቻል የህገ-ወጥ ግብይትን ለመግታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል፣ የክልል፣ የዞን እና የወረዳ አካላት ጋር በመቀናጀት የተጠናከረ የቁጥጥር ሥርዓት እንዲዘረጋና ተግባራዊ እንዲሆን ማስተባበር ይጠበቅበታል፤

75. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት በኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ምስራቅ ወለጋ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች እና በማና፣ ጎማና በደሌ ወረዳዎች እንዲሁም በደቡብ ክልል ሲዳማ፣ ጌዲኦ፣ ቤንች ማጂ እና ማሻ ዞኖች እና ዳሌ፣ ዬኪ፣ ይርጋጨፌ እና ግንቦ ወረዳዎች ውስጥ ከሚገኙ የግብርናና የግብይት ቢሮዎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ-መጠይቅ ከቀበሌ እስከ ክልል ድረስ ህገ-ወጥ ግብይት ለመቆጣጠር ከየሴክተር መስሪያ ቤቶች ተወጣጥተው የተቋቋሙ ግብረ-ኃይሎች ቢኖሩም የግብረ-ኃይሉ አባላት ለመደበኛ ስራ ትኩርት በመስጠት ህገ-ወጥ ግብይት መቆጣጠርን እንደራስ ሥራ አድረጎ አለማየት፣ የመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከላት በተሟላ መልኩ ባለመገባንታቸው እና ኬላዎች በተጠናከረና አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች ባለመቋቋማቸው እና

ሥራው ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ በተጠናከረ ቅንጅት እንዲሰራ በንግድ ሚኒስቴር ወቅታዊና ተከታታይነት ያለው የማስተባበር ሥራ ባለመሰራቱ የህገ-ወጥ ግብይቱን የመቆጣጠር ሥራ በተጠናከረ መልኩ እየተሰራ ነው ለማለት እንደማያስችል ገልጸዋል፡፡

76. በተጨማሪም በኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር ዞን በበደሌ ወረዳ፣ በምዕራብ ወለጋ ዞንና ምስራቅ ወለጋ ዞን በህገ-ወጥ መንገድ ሲጓጓዙ በኬላዎች ላይ ተይዘው ወደ ፍትህ አካላት የቀረቡ ምርቶች የቁጥጥር ሥራው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ባለመጠናከሩ ምክንያት ያለምንም ማጣራት ለባለንብረቶቹ ተመልሰው በመሰጠታቸው የህገ-ወጥ ግብይቱ እንዲስፋፋ መንገድ ሊከፍት እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

77. በተመሳሳይ መልኩ በናሙና ተመርጠው ከታዩት የግብረና ምርት ላኪዎች ጋር በተደረገው ቃለ-መጠይቅ ቀይ በሎቄ በህገ-ወጥ መንገድ ወደ ኬንያ እንደሚጓጓዝና ጉዳዩን ለሚመለከታቸው አካለት ቢያሳውቁም መፍትሄ ሊገኝ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

78.ስለጉዳዩ በንግድ ሚኒስቴር የግብርና ምርት ግብይት ዳይሬክቶሬት የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የኮንትሮባንድ ችግር በፌዴራል ጀምሮ እስከ ቀበሌ አሠራር ተቀምጦለትና ግብረ ኃይል ተደራጅቶ በዋናነት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አስተባባሪነት እየተከናወነ እንደሚገኝ ሆኖም ኮንትሮባንድ ችግር እንዳለ በሚኒስቴር መስሪያቤታችንም ስለሚታወቅ ከኮሚቴው ጋር እየተሰራበት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

79. የንግድ ሚኒስቴር ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች በዘመናዊ እና ህጋዊ የግብይት ሥርዓት ውስጥ ገብተው የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ በማሟላት እንዲያቀርቡ ለማስቻል የህገ-ወጥ ግብይትን ለመግታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል፣ የክልል፣ የዞን እና የወረዳ አካላት ጋር በመቀናጀት የተጠናከረ የቁጥጥር ሥራ አለመካሄዱ ሀገሪቱ በዓለም ገበያ በጥራት ተወዳዳሪ እንዳትሆን እና በዘርፉ የተሻለ የውጭ ምንዛሪ እንዳታገኝ ሊያደርግ እና የህገ-ወጥ ግብይትን በማስፋፋት የህጋዊ ነጋዴዎችን ውጤታማነት እና የሥራ ቀጣይነት /sustainability/ ላይ የጎላ ተጽዕኖ ያስከትላል፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

- ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች ተገቢውን የጥራት ደረጃ እንዲያሟሉ በየምርቶቹ ባህሪና ዓይነት ከማሳ እስከ ማዕከል ባለው ሰንሰለት ቼክሊስት በማዘጋጀት የተጠናከረ ወቅታዊ የጥራት ክትትል በየደረጃው በሚገኙ አካላት በተለይ ወደ ዘመናዊ ግብይት ባልገቡ ምርቶች አለመጠናከሩ፣

- በየወረዳዎቹ የተመደቡት የጥራት ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ቁጥር በቂ አለመሆኑና ለስራቸው የሚያስፈልጋቸው የሎጂስትክ አቅርቦት አለመሟላቱ፤

- በኦሮሚያና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል በሚገኙ አንዳንድ ወረዳዎች ያልደረሰ ቡና ወይም ጥቁር ቡና ለገበያ መቅረቡ፤

- በኦሮሚያ ክልል እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል በሚገኙ አንዳንድ ወረዳዎች የሚገኙ የቡና አምራች አርሶ አደሮች ቡናን በመኪና መንገድ ላይ አስጥተው የሚያደርቁ መሆኑ፤

- አንዳንድ ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች የግብይት አዋጅና ደንብ ያልወጣላቸው መሆኑ እና ምርቶቹ በሚመረቱበት አከባቢ የመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት አለመገንባቱ፣

- የጥራትና ደረጃ ማዕከላት ወደ ውጭ ገበያ በሚቀርቡ በሁሉም የግብርና የምርት አይነቶች እና የግብርና ምርቶቹ በሚመረቱበት በቅርብ አካባቢ እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ አለመደረጋቸው፤

- የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለውጭ ሀገር ገበያ በአቅራቢዎች የሚቀርበው የግብርና ምርት ያገኘውን ደረጃና በጥራቱ ላይ የታዩ ጉድለቶች እንዲሻሻሉ ለማስቻል ግብረ መልስ (feed back) ለግብርና ባለሙያዎች እና ለአርሶ አደሮች እንዲደርሳቸው አለመደረጉ፤

- የግብርና ምርት ላኪዎች (exporters) ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚገዙት ምርት የኪሎ ጉድለት የሚያሳይ መሆኑ፣ በተገዛው የጥራት ደረጃ ልክ የማይደርሳቸው መሆኑ እና

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የግብርና ምርቶች የመገበያያ ዋጋ ከዓለም የገበያ ዋጋ ጋር የማይጣጣም መሆኑ እንዲሁም የመጋዘን አገልግሎት አስጣጥ ቀልጣፋ አለመሆኑ፤

- የንግድ ሚኒስቴር ወደ ዘመናዊ የግብይት ስርዓት ያልገቡና በውጭ ሀገራት ገበያዎች የሚፈለጉ የግብርና ምርት አይነቶችን እና በየሀገራቱ የሚፈለገውን የጥራት ዓይነት እና መጠን በማጥናት መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመተንተንና በማጠናከር ምርቶቹ ሊመረቱባቸው ለሚችሉ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች የግብርናና የግብይት ቢሮዎች እንዲሁም ለላኪዎች አንዲደርሳቸው አለመደረጉ፤
- ወደ ውጭ ሀገር ገበያ የሚላኩ ዋና ዋና የግብርና ምርቶችን አስመልክቶ የገበያ ፍላጎትና የዋጋ ትንበያ ጥናት በንግድ ማኒስቴር አለመካሄዱ፤
- የንግድ ሚኒስቴር በዘመናዊ የኢንፎርሜንሽን ቴክኖሎጂና በባለሙያ የተደራጀ ለግብርና ምርቶች የውጭ ግብይት ወሳኝ የሆኑ የአለም አቀፍ መረጃዎችን በመሰብሰብና በማጠናከር በዘርፉ በግብይት እና በምርት ሂደት ለተሰማሩ አካላት ወቅታዊ መረጃ አለማቅረቡና ለዘርፉ አገር አቀፍ የመረጃ ቋት ማዕከል በመሆን አለማገልገሉ፤
- የንግድ ሚኒስቴር በየክልሉ ካሉ የውጪ ንግድ ድጋፍ ኮሚቴዎች ጋር ወቅታዊ የውይይት መድረክ አለመዘጋጀቱ፤
- የንግድ ሚኒስቴር ለውጭ ንግድ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን በጥራት ለማቅረብ የሚያግዙ የጆኒያ፣ ፒፒ ከረጢት እና የቡና ማስጫ አልጋ ለመስራት የሚያገለግል ሽቦ አቅራቢዎችን በማስተባበር አርሶአደሮች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ አለማድረጉ እና እጥረት መከሰቱ፤
- የንግድ ሚኒስቴር ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች በዘመናዊ እና ህጋዊ የግብይት ሥርዓት ውስጥ ገብተው የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ በማሟላት እንዲያቀርቡ ለማስቻል የህገ-ወጥ ግብይትን ለመግታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል፣ የክልል፣ የዞን እና የወረዳ አካላት ጋር በመቀናጀት የተጠናከረ የቁጥጥር ሥራ አለመካሄዱ፣ በንግድ ሚኒስቴር ቀጥተኛ ክትትል የሚደረግባቸው የግብርና ምርቶች የውጭ ንግድ ማስፋፊያ ሥርዓት አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጉታል፡፡ ስለሆነም ከላይ የተመለከቱትን ድክመቶች ለማሻሻል አስተዋጾ የደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሀሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## ማሻሻያ ሃሳብ

- የንግድ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው የክልል፣ የዞን እና የወረዳ አካላት ጋር በመተባበር ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች ተገቢውን የጥራት ደረጃ እንዲያሟሉ በየምርቶቹ ባህሪና ዓይነት ከማሳ እስከ ማዕከል ባለው ሰንሰለት ቼክሊስት በማዘጋጀት የተጠናከረ እና ወቅታዊ የጥራት ክትትል መደረጉን መከታተል እና መደገፍ ይኖርበታል፡

- የንግድ ሚኒስቴር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ከፌዴራል እና ከክልል አካላት ጋር በመተባበር ለግብርና ባለሙያዎች፣ ለአርሶአደሮች እና ለግብርና ምርት አቅራቢዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ በመስጠት ያልደረሰ ቡና ወይም ጥቁር ቡና ለገበያ እንዳይቀርብ እና አምራች አርሶ አደሮች ቡናን በመኪና መንገድ ላይ አስጥተው እንዳያደርቁ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል፤

- የንግድ ሚኒስቴር ለውጭ ገበያ ለሚቀርቡ የግብይት አዋጅ እና ደንብ ላልወጣላቸው የግብርና ምርቶች አዋጅና ደንብ እንዲወጣላቸው እና ምርቶቹ በሚመረቱበት አካባቢ የመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከል እንዲገነቡ አስፈላጊውን ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፤

- የንግድ ሚኒስቴር በፌዴራል እና በክልል ከሚገኙ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የጥራትና ደረጃ ማዕከላት ወደ ውጭ ገበያ በሚቀርቡ በሁሉም የግብርና የምርት አይነቶች እና የግብርና ምርቶቹ በሚመረቱበት አካባቢ እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ አስፋለጊውን ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል፤

- የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለውጭ ሀገር ገበያ በአቅራቢዎች የሚቀርበው የግብርና ምርት ያገኘውን ደረጃና በጥራቱ ላይ የታዩ ጉድለቶች እንዲሻሻሉ ለማስቻል ግብረ መልስ (feed back) ለግብርና ባለሙያዎች እና ለአርሶ አደሮች እንዲደርሳቸው ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት እንዲዘረጋ ንግድ ሚኒስቴር ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፤

- የግብርና ምርት ላኪዎች (exporters) ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚገዙት ምርት የኪሎ ጉድለት እንዳይኖረው፣ በተገዛው የጥራት ደረጃ ልክ እንዲደርሳቸው እና የኢትዮጵያ ምርት

ገበያ የግብርና ምርቶች የመገበያያ ዋጋ ከዓለም የገበያ ዋጋ ጋር እንዲጣጣም ለማደረግ እንዲሁም የመጋዘን አገልግሎት አስጣጥ ቀልጣፋ እንዲሆን ንግድ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ጋር በቅርበት በመስራት ችግሮቹ እንዲፈቱ ማድረግ ይኖርበታል፤

- የንግድ ሚኒስቴር ወደ ዘመናዊ የግብይት ስርዓት ያልገቡና በውጭ ሀገራት ገበያዎች የሚፈለጉ የግብርና ምርት አይነቶችን በማጥናት መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመተንተንና በማጠናከር ምርቶቹ ሊመረቱባቸው ለሚችሉ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች የግብርናና የግብይት ቢሮዎች እንዲሁም ለላኪዎች እንዲደርሳቸው በማድረግ ምርቶቹ በሚፈለገው ጥራትና መጠን ተመርተው ለውጭ ሀገር ገበያ እንዲርሱ ማድረግ ይኖርበታል፤
- የንግድ ሚኒስቴር ወደ ውጭ ሀገር ገበያ የሚላኩ ዋና ዋና የግብርና ምርቶችን የገበያ ፍላጎትና የዋጋ ትንበያ ጥናት በማካሄድ ለአርሶ አደሮችና ለገበያ ተዋኒያኖች እንዲደርስ ማድረግ ይኖርበታል፤
- የንግድ ሚኒስቴር በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ባለሙያ የተደራጀ ለግብርና ምርቶች የውጭ ግብይት ወሳኝ የሆኑ የአለም አቀፍ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናከር በዘርፉ በግብይት እና በምርት ሂደት ለተሰማሩ አካላት ወቅታዊ መረጃ በማቅረብና ለዘርፉ አገር አቀፍ የመረጃ ቋት ማዕከል በመሆን ማገልገል ይኖርበታል፤
- የንግድ ሚኒስቴር በየክልሉ ካሉ የውጭ ንግድ ድጋፍ ኮሚቴዎች ጋር ወቅታዊ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት የግብርና ምርቶችን በማምረት እና ወደ ውጭ ገበያ በመላክ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጋራ የሚፈቱበት አሰራር እንዲፈጠር ማድረግ ይጠበቅበታል፤
- የንግድ ሚኒስቴር ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን በጥራት ለማቅረብ የሚያግዙ የጆኒያ፣ ፒፒ ከረጢት እና የቡና ማስጫ አልጋ ለመስራት የሚያገለግል ሽቦ አቅራቢዎችን በማስተባበር አርሶአደሮች በተመጣጣኝ ዋጋና በበቂ መጠን እንዲያገኙ ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፤
- የንግድ ሚኒስቴር ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች በዘመናዊ እና ህጋዊ የግብይት ሥርዓት ውስጥ ገብተው የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ በማሟላት እንዲቀርቡ ለማስቻል የህገ-ወጥ ግብይትን ለመግታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል፣ የክልል፣ የዞን እና የወረዳ አካላት ጋር በመቀናጀት የተጠናከረ የቁጥጥር ሥራ እንዲካሄድ ማድረግ ይጠበቅበታል።

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና ጉዳዩ በሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ለተደረገልን የስራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

### ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፡ የንግድ ሚኒስቴር

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria) |
|---|---|---|
| | በንግድ ሚኒስቴር ቀጥተኛ ክትትል የሚደረግባቸው የግብርና ምርቶች የውጭ ንግድ ማስፋፊያ ሥርዓት እና ውጤታማነቱን መገምገም | |
| 1 | ለዓለም ገበያ ሊላኩ የሚችሉ የግብርና ምርቶች ላይ ቁጥጥር፣ ክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ለማድረግ የሚያስችል አሠራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን እና አፈፃፀሙን መገምገም፤ | |
| | 1.1. ወደ ውጭ በሚላኩ የግብርና ምርቶች ላይ የሚደረገውን የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓትን መገምገም፤ | 1 ወደ ውጭ የሚላኩ የግብርና ምርቶችን ለመቆጣጠርና ለመከታተል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፤ |
| | | 2 የንግድ ሚኒስቴር በሀገሪቱ ወደ ውጭ በሚላኩ በሁሉም ዓይነት የግብርና ምርቶች የግብይት ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረግ ይኖርበታል፤ |
| | | 3 የንግድ ሚኒስቴር የሀገሪቱን የግብርና ምርት ተቀባይ አገሮች የሚፈልጉትን ጥራትና ደረጃ በመከታተል ለልማት ዘርፍና ለገበያ ተዋንያኖች በማድረስ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ክትትል ሊደረግ ይገባል፤ |

| | | |
|---|---|---|
| | | 4 የንግድ ሚኒስቴር አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች እንዲሁም በግብርና ልማት የተሰማሩ ድርጅቶችና የንግዱ ህብረተሰብ በአለም ገበያ ውስጥ በዋጋና በጥራት ተወዳደሪ ሊሆኑ የሚችሉባቸውን የግብርና ምርቶችን ለይተው እንዲያውቁ ለያደርግ ይገባል፤ |
| | | 5 የንግድ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የግብርና ግብይት በተሻለ ማምረት የሚያስችል ኢንስቲትውሽን ሊገነባ ይገባል፤ |
| | | 6 የንግድ ሚኒስቴር የምርት አቅርቦትና የምርት ጥራትን ለማሻሻል ተዋንያኖችን በተሟላ ሁኔታ ሊያሳትፍና ሊከታተል ይገባል፤ |
| | | 7 የንግድ ሚኒስቴር ቀጥተኛ ክትትል የሚያደርግባቸው ወደ ውጭ ገበያ የሚላኩ የግብርና ምርቶችን ወደ ዘመናዊ የግብይት ስርዓት ማዕቀፍ ውሰጥ እንዲካተቱ ማድረግ ይጠበቅበታል፤ |
| | | 8 የንግድ ሚኒስቴር ወደ ውጪ የሚላኩ የግብርና ምርቶችን በየምርቶቹ ባህሪና ዓይነት ከማሳ እስከ ማዕከል ባለው ሰንሰለት ቼክሊስት በማዘጋጀት ወቅታዊ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፣ |
| | | 9 የንግድ ሚኒስቴር የጥራትና ደረጃ ማዕከላት ምርቱ በሚመረትባቸው አካባቢዎች እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ በማድረግ የማዕከላቱን ሥራ ሊያስተባብር ይገባል፤ |
| | 1.2 ወደ ውጭ በሚላኩ የግብርና ምርቶች ላይ የሚደረገው | 10 የግብርና ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ ሂደት የህበረት ስራ ማህበራት ሚና |

| | | |
|---|---|---|
| | የድጋፍ ሥርዓትን መገምገም፤ | እንዲጎለብት የንግድ ሚኒስቴር አስፈላጊውን ድጋፍ ሊሰጥ ይጋባል፤ |
| | | 11 የንግድ ሚኒስቴር የግብርና ምርት አምራቾችና ላኪዎችን ለማበረታታት የሚያስችል የማበረታቻ ዓይነት እያጠና ማቅረብ ሲፈቀዱም ተግባራዊነቱ ክትትል ሊደረግ ይገባል፤ |
| | | 12 የንግድ ሚኒስቴር ወደ ዉጪ የሚላኩ የግብርና ምርቶችን በየምርቱ ዓይነት ከማሳ እስከ ማዕከል ባለው ሰንሰለት ቼክሊስት በማዘጋጀት ድጋፍ የሚሹ ተግባራትን ለይቶ አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፤ |
| | | 13 ወደ ውጭ የሚላኩ  የግብርና ምርቶች ንግድ ውስጥ ጉልህ ሚና ለሚጫወቱና ለንግድ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ መስሪያ ቤቶችን በግብርና ምርት ንግድ ዙሪያ የሚከሰቱትን የአፈጻጸም ችግሮች በወቅቱ እንዲፈቱ ድጋፍ ሊያደረግ ይገባል፤ |
| | | 14 የንግድ ሚኒስቴር የላኪዎችን የፋይንናስ አቅም ለማጎልበት በመንግሥት በኩል የብድር አቅርቦት ማዋቅር ሊያመቻችና በወቅቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊደረግ ይገባል፤ |
| | | 15 የንግድ ሚኒስቴር ለላኪ ድርጅቶች የኤክስፖርት ቢዝነስ ፕላን እንዲያዘጋጁና በዚሁ በመመሥረትም የአፈፃፀም ደረጃቸውን በየጊዜው በመገምገም የማሻሻያ እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደረግ ይገባል፤ |
| | | 16 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የግብርና ምርቶች |

| | | |
|---|---|---|
| | | አቅርቦትንና የኤክስፖርት እንቅስቃሴውን ለመደገፍ በመስክ በመገኘት ክትትል በማድረግ፣ላጋጠሙ ችግሮችም መፍትሄ የማፈላለግ ሥራ ሊከናወን ይገባል፤ |
| 2 | ለዓለም ገበያ ሊላኩ ለሚችሉ የግብርና ምርቶች የውጭ ሀገር ገበያ ለማፈላለግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን፣ አፈፃፀሙን እና ውጤታማነቱን መገምገም፤ | 17 የንግድ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ኤምባሲዎች አማካኝነትና በቀጥታ በንግድ ትርኢቶች ላይ በመሳተፍ የግብርና ምርቶችን ሊያስተዋውቅ ይገባል፤ |
| | | 18 የንግድ ሚኒስቴር በኢምባሲዎች በኩል በውጪ ምርቶች ኤክስፖርት ሂደት ከተቀባይ ሀገሮች ግብረ መልስ የሚገኝበትን ሥርዓት በመዘረጋት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፤ |
| | | 19 የንግድ ሚኒስቴር የግብርና ምርቶችን የሚያስተዋውቁ በራሪ ጽሁፎች/ፖስተሮች እና ፊልሞችን አዘጋጅቶ ለተቀባይ አገራት ሊሰራጭ ይገባል፤ |
| | | 20 የንግድ ሚኒስቴር የቢዝነስ ልኡካን/Business Delegation/ በማዘጋጀት የሀገሪቱን የግብርና ምርቶች ለውጭ ሀገራት ሊያስተዋውቅ ይገባል፤ |
| | | 21 የንግድ ሚኒስቴር በውጭ ሀገራት ገበያ የሚፈለጉ የግብርና ምርት ዓይነቶችን በማጥናት ለሀገራችን ላኪዎችና ለሚመለከታቸው አካላት መረጃ ሊያስተላልፍ ይገባል፤ |
| | | 22 የንግድ ሚኒስቴር የሀገሪቱን ምርቶች |

| | | |
|---|---|---|
| | | በመቀበል የሚታወቁ ሀገራትን የንግድ ማህበረሰብ አባላትና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን አካላት ወደ አገር ውስጥ በመጋበዝ ምርቶችን ሊያስተዋውቅ ይገባል |
| | | 23 የንግድ ሚኒስቴር የሀገሪቱን የግብርና ምርቶች በመቀበል የሚታወቁ ሀገራትን ከሚፈልጉት የምርት አይነትና ሙሉ አድራሻ በማሰባሰብ ለላኪዎች እንዲደርስ ሊደረግ ይገባል፤ |
| | | 24 የንግድ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በውጭ ሀገራት በሚዘጋጁ ትሬዮድ ፌዬሮችና ኤግዚቢሽኖች ላይ የሀገሪቱን የግብርና ምርት ላኪዎች እንዲሳተፉ በማድረግ ምርቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁና አስፈላጊውን የገበያ መረጃ እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፤ |
| | | 25 ንግድ ሚኒስቴር በሀገሪቱን ውስጥ ትሬድ ፌሮች/Trade Fair/ና ኤግዝቪሽኖች በማዘጋጀት የግብርና ምርቶችንና ላኪዎችን ለተቀባይ ሀገራትና መሰል ሀገሮች ሊያስተዋውቁ ይገባል፤ |
| | | 26 ንግድ ሚኒስቴር ነባር የውጭ ገበያዎችን ለማቆየትና አዳዲስ ገበያዎችን ሰብሮ ለመግባት በተከታታይ የውጭ ሀገር ገበያ የማፈላለግ ሥራ ሊከናወን ይገባል፤ |
| 3 | ለዓለም ገበያ ሊላኩ የሚችሉ የግብርና ምርቶች የመረጃ አያያዝና ስርጭት ሥርዓት መገምገም፤ | 27 የንግድ ሚኒስቴር ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት በመዘርጋት ለወጭ ንግድ እድገት አሰፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መያዝና ለሚመለከታቸዉ አካላት በወቅቱ |

| | | |
|---|---|---|
| | | ማስተላለፍስ ይጠበቅበታል፤ |
| | | 28 የንግድ ሚኒስቴር ወደ ውጭ የሚላኩ ዋና ዋና የግብርና ምርቶችን የገበያ ፍላጎትና የዋጋ ትንቢያ ጥናት ሊካሄድ እና ውጤቱንም ለሚመለከተቸው አካላት ሊሰራጭ ይገባል፤ |
| | | 29 የንግድ ሚኒስቴር በአለም አቀፍ የመረጃ መረብ ጋር በመዋዋል ተገቢውን መረጃ በመሰበሰብና በመተንተን ለተዋኒያኑ ማድረስ ይገባል፤ |
| 4 | የውጭ ንግድ ማስፋፊያ በተመለከተ ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት መካከል ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር መገምገም፣ | 30 የንግድ ሚኒስቴር በክልል ከተደራጁ የኤክስፖርት ልማት ደጋፍ ኮሚቴ ጋር በአፈጻጸም ሂደቶች ዙሪያ በጋራ የውይይት መድረክ ሊዘጋጅ ይገባል፤ |
| | | 31 የንግድ ሚኒስቴር ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን የትራንስፖርት አቅርቦት ችግር እንዳይገጥማቸው ከትራንስፖርት ሚኒስቴር ጋር በመሆን ሥልት በመቀየስና አፈጻጸሙን በየጊዜው በመከታተል በሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ ወቅታዊ ምላሽ ሊሰጥበት ይገባል፤ |
| | | 32 የንግድ ሚኒስቴር የብድር አቅርቦት ሪፖርት ምርት ከመድረሱ በፊት በባንኮች ለግብርና ምርት ላኪዎች እንዲመቻች አስፈለጊውን ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግና አፈጻጸሙን በየጊዜው በመከታተል በሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ ወቅታዊ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፤ |
| | | 33 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወደ ውጭ የሚላኩ የግብርና ምርቶችን በሚመለከት ከጉምሩክ |

| | | |
|---|---|---|
| | | የሚፈለጉ ዶክመንቶች  በወቅቱ ለሚፈልገው አካል  እንዲሰጡ ሊያደርግ ይገባል፤ |
| | | 34 የንግድ ሚኒስቴር የጋራ መድረኮች በማዘጋጀት ከላኪዎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ማካሄድና ለሚከሰቱ ችግሮች የጋራ መፍትሄ ማፈላለግ ይገባል፤ |
| | | 35 የንግድ ሚኒስቴር ከክልል ንግድ ቢሮዎች ጋር ቀጣይነት ያለውና ወቅታዊ የሆነ የመረጃ ፍሰትና ልውውጥ እንዲኖር ሊያደረግ ይገባል፤ |
| | | 36 የንግድ ሚኒስቴር ለአርሶ አደሩ በቂ የጆኒያ እና የፒፒ ከረጢት አቅረቦት በተመጣጣኝ ዋጋ ከአቅራቢው እንዲያገኙ ከጆኒያና ፒፒ ከረጥት አምራች ድርጅቶች ጋር የመቀናጀትና የማስተሳሰር ሥራ ሊሰራ ይገባል፤ |
| | | 37 በግብርና ምርት ግብይትና ኤክስፖርት ለተለያዩ ድጋፍ ሰጪ መ/ቤቶችና ባለድርሻ አካላት በሚደረግ የምክክር መድረክ አጠቃላይ በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚነሱትን ችግሮች በተቀናጀ መልኩ እንዲፈቱ የማስተባበር ተግባር በንግድ ሚኒስቴር ሊከናወን ይገባል፤ |
| | | 38 የንግድ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አከላት ጋር በመተባበር ወደ ውጭ የሚላኩ የግብርና ምርቶችን በየምርቶቹ ባህሪና ዓይነት ከማሳ እስከ ማዕከል ባለው ሰንሰለት ቼክሊስት በማዘጋጀት ወቅታዊ ክትትል |

| | | |
|---|---|---|
| | | ማድረግ ይኖርበታል; |
| | | 39 የንግድ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አከላት ጋር በመተባበር የግብርና ምርቶች የህገወጥ ግብይትን በእቅድና በቅንጅት የመቆጣጠር ጥረት ሊኖር ይገባል፤ |
| | | 40 የንግድ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመመተባበር የግብርና ምርቶችን በወቅቱ ወደ ገበያ እንዲደርስ ሊደረግ ይገባል፤ |